ደጃች ረታና ቤተሰቡ
ቤት መጻሕፍት

## ክርስቶስ በኢስላም (በቁርዓን)

# ክርስቶስን ከቁርዓን ጋር ምን አገናኘው?

መጽሐፍ ቅዱስና ሙሐመድ አይተዋወቁም

አዎ ኢየሱስ ፈጣሪ ነው የሚሉት መጻሕፍት
በዚሁ በጽሐፍ ተካትተዋል።

ከመምህር ኪዳነማርያም ጌታሁን
ለሸህ አህመድ ዲዳት የተሰጡ መልሶች ናቸው።

1991 ዓ.ም.

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

በ1999 ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

3. አይሁዶች ተገረሙ ........ 42
4. የመሢሕ ክርስቶስ ልደት ........ 44
5. የመጀመሪያው ተአምር ........ 46
6. እማዬ! ወይስ አንች ሴት! ........ 53
7. ጥብቅና ለኢየሱስ ........ 56

## አምስተኛ ምዕራፍ
## ወንጌላዊውና ቁርዓናዊው ትረካ

1. ቆይታ ከቄሱ ጋር ........ 58
2. ሰማይና ምድር ........ 60
3. የአዳም ቢጤና የጳውሎስ ፈጠራ ........ 65
4. ሳውል ከአሪት ወደ ወንጌል . . ........ 73
5. የአምላክ ልጆች ........ 75
6. ምሥጢረ ሥላሴ ........ 78
7. ምሥጢረ ሥጋዊ ........ 80
8. ከሥላሴ አንዱ ወልድ ለምን ሰው ሆነ? ........ 85

## ስድስተኛ ምዕራፍ
## ምላሽ ለሕዝበ ክርስቲያን ውዥንብር

1. የትንሣኤው ቀን ጥያቄና የኢየሱስ ምላሽ ........ 93
2. ከቶውንም አምላክ ነኝ አላለም ........ 95

## ሰባተኛ ምዕራፍ

በመጀመሪያው ........ 98

## ስምንተኛ ምዕራፍ

ምን ቀረ? ........ 102
ማስታወሻዎች ........ 114



## መቅድም

## የ666 መርሐ ግብር (ፕሮግራም)

በዮሐንስ ራዕይ ምዕራፍ 13 ቁ. 1- 18 ታሪኩ የተጻፈለት ወንጌላዊው ዮሐንስ በደሴተ ፍጥሞ ታስሮ ሳለ ከባሕር ሲወጣ ያየው አስገራሚ ዓውሬ ባሁኑ ጊዜ ሥልጣን ከጨበጠ ጥቂት ዓመታት አልፈዋል፣ "ዓውሬው አስር ቀንዶች ሰባት ራሶች አሉት፣ በቀንዶቹ ላይ አስር አክሊሎች ተቀምጠዋል፣ በስተጀርባው "የዛቻና የስድብ" መፈክር በታላላቅ ፊደሎች ተጽፎ ከሩቁ ይነበባል፣ መፈክሩ "ክርስቲያኖችን እናጥፋቸው" የሚል ነው፣ 42 ወራት (ሦስት ዓመት ከመንፈቅ) ያህል የፈለገውን ያደርግ ዘንድ ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

በምድር ላይ ያሉት ስማቸው በታረደው በግ የሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፈው ሁሉ ይሰግዱለታል፣ ጆሮ ያለው ይስማ፣ ማንም በሰይፍ የገደለ በሰይፍ ይሞት ዘንድ ግድ አለው፣ በዚህ ጊዜ ነው የቅዱሳን ክርስቲያኖች ትዕግስትና ሃይማኖት የሚታወቀው፣ ዓውሬው በምድር ላይ ያሉትን ሁሉ ያስት ዘንድ ከሰማይ እሳትን እስከማውረድ ተአምራት ያደርጋል" ይላል።

ከዕለታት አንድ ቀን ዓውሬው አስቸኳይ ስብሰባ ጠራ፣ ታላቁም ታናሹም ድሆችም ሀብታሞችም ጌቶችም ባሮችም በስብሰባው ላይ እንዲገኙ ተደረገ፣ የስብሰባው አዳራሽ ስፋት የምድርን ግማሽ ይሸፍናል፣ ዓውሬው ስብሰባውን ለመምራት የመዓረግ ልብሱን ለብሶ በሰገነቱ ላይ ተገኘ፣ የስብሰባው አጀንዳዎች ሁለት ሲሆኑ አንደኛው 666 የተሰኘውን የራሱን ልዩ ዓርማ ከሕዝብ ጋር ለማስተዋወቅ ነው፣ ሁለተኛው ደግሞ ክርስቲያኖች ከገጸ ምድር የሚጠፉበትን ስልታዊ መንገድ ተነጋግሮ ለመወሰን ነው።

በመርሐ ግብሩ መሠረት በተወሰነው ሰዓት ስብሰባው ቀጠለ፣ አዳራሹ በሕዝብ ተሞልቷል፣ ዓውሬው በሰገነቱ ላይ እንደተቀመጠ

www.ethiopianorthodox.org

## መግቢያ

# ክርስቶስን ከቁርዓን ጋር ምን አገናኘው?

## (ቁርዓን ስለ ክርስቶስ ምን ያውቃል?)

"ክርስቶስ በኢስላም" በሚል ርዕስ ከሸህ አህመድ ዲዳት በ8 ምዕራፎች ከ 50 በላይ በሆኑ ንዑሳን ክፍሎች ተከፋፍሎ የተዘጋጀውን መጣጥፍ አነበብሁት፤ዝግጅቱ ቀላል አልነበረም፤ ለጊዜው የማይዋጥ ማላመጥ ሆኖብኝ ነበር፤ ሆኖም "ብርቱን ሥጋ በብርቱ መንጋጋ" ነውና እግዚአብሔር በፈጠረልኝ ክራንቻዎቼ ሁሉ በመጠቀም ገርድፌና ሰልቄ አጣጣምኩት፤

"ይህችን መጽሐፍ እንካ ብላት፤ ላፍህ እንደማር ጣፋጭ ትሁን፤ ሆድህን ግን ትምረረው"፤ ራዕይ 10 ቁ.9-10፤ እስልምናና ክርስትና የፍልስፍናም ሆነ የዓላማ አንድነት የላቸውም፤ ሁለቱ እምነቶች የዓላማና የፍልስፍና አንድነት ባይኖራቸውም የክርስትና ሃይማኖት ዓለምአቀፍ ሃይማኖት ሆኖ 2000 ዓመታት ያህል አስቆጥሯል፤ እስልምናም እንደዚሁ ዓለማቀፍ ሃይማኖት ሆኖ ከ1400 ዓመታት በላይ አስቆጥሯል፤ በመካከላቸው የ600 ዘመን ልዩነት አለ፤

እነዚህ ሁለቱ የኅብረተሰብ ክፍሎች (ሙስሊሙና ክርስቲያኑ) የሃይማኖት መመሪያዎቻቸውን (ቁርዓንንና ወንጌልን) ጠብቀው በመቻቻል እየተረዳዱ ይህን ያህል ዘመን ሊኖሩ ችለዋል። ይሁን እንጂ ባሁኑ ጊዜ እንደ አህመድ ዲዳት ያሉ የእስላም አፈቀላጤዎች



መጽሐፍ ቅዱስን እየበረዙና እየከለሱ ፍጡርን ከፈጣሪ ጋር እያወዳደሩና እያስተካከሉ የእስልምና ሃይማኖት ከሁሉም በላይ ነው በማለት መጣጥፎችን እያዘጋጁ ሲያሰራጩ ይታያሉ፤ ይኸውም በዓለም ላይ እንደ ኤድስ በሽታ እየተስፋፋ ያለውን አክራሪነት ወደ አፍሪካ ቀንድ ለመጋበዝ ጥርጊያ መንገድን እያዘጋጁ ነው፤ አክራሪነት ግን ለማንም ለምንም አይበጅም።

የውጭ አገር ኢንቨስተሮች ወደ አገራችን ገብተው ገንዘባቸውን አፍስሰው ራሳቸውን እየጠቀሙ አገሪቱን እንዲጠቅሙ መንግሥት በሰጠው ሰፊ ዕድል መሠረት በልዩ ልዩ የልማት ዘርፍ ተሰማርተው ሲንቀሳቀሱ የደቡብ አፍሪካው ኢንቨስተር አህመድ ዲዳት ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶ ያፈሰሰው ጥሬ ሀብት ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ መጣጥፍ ነው፤ ይሁን እንጂ በጨዋነቱ መላው ዓለም ያደነቀው የኢትዮጵያ ህዝብ (ሙስሊሙና ክርስቲያኑ) ከአህመድ ዲዳት የቀረበለትን በረከተ መርገም መጣጥፍ እንደማናቸውም መጽሔትና ጋዜጣ አንብቦ በትዝብት አለፈው እንጂ ባሕርዩን አልቀየረውም፤ ጨዋነቱን አልበረዘውም፤ ሆኖም የኦሪቱ ሕግ "ዓይን በዓይን ጥርስ በጥርስ" ስለሚል ከአህመድ ዲዳት ለተጻፈው መጣጥፍ ወረቀቱን በወረቀት መመለስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ አንባቢው የሰውየውን ተነሳሽነትና አፍራሽ ተልዕኮ አመዛዝኖ እንዲረዳው መልስ ሰጥቼበታለሁ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባንድ ወቅት ሲያስተምር ፈሪሳውያን ሊፈታተኑት ፈልገው "ለቄሳር ግብር መስጠት ይገባልን? ወይስ አይገባም?" አሉት፤ እርሱም አሳባቸውን አውቆ እናንተ ግብዞች ለምን ትፈትኑኛላችሁ? እስቲ ገንዘቡን አሳዩኝ አላቸው፤ የቄሳር ስምና የእግዚአብሔር ስም የተፃፈበትን ገንዘብ አሳዩት፤ የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሐር ስጡ አላቸው፤ እነርሱም በመልሱ እየተደነቁ ትተውት ሄዱ" ይላል ማቴ. 22 ቁ. 15።

እንደዚሁም ቁርዓን ለክርስቶስ ወንጌልም ለሙሐመድ ገጸ በረከት ሆነው ሊቀርቡ አይችሉም፤ ወንጌል ለክርስቲያኑ ኅብረተሰብ



www.ethiopianorthodox.org

የተሰጠ መለኮታዊ መመሪያ ነው፣ ቁርዓንም ለሙስሊሙ ኅብረተሰብ የተሰጠ ሃይማኖታዊ መመሪያ ነው፣ ስለዚህ ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን የሃይማኖት መመሪያ ጠብቀው ኅብረተሰባቸውን እየመከሩና እያስተማሩ መኖር እንጂ አንዱ በሌላው የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እየገቡ ሁከትን የሚያነሳሳ ፖንፍሌት መርጨት የሰይጣን ሥራ ነው፤ ይህንም ያደረጉት ድንበር ዘለል አክራሪዎች ናቸው እንጂ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች እንዳልሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

ሁለት የተለያዩ የእህል ዓይነቶች ባንድ ማሳ ውስጥ ተቀላቅለው ቢዘሩ ውህደት አይኖራቸውም፣ ለምሳሌ ስንዴና ገብስ ባንድነት ቢዘሩ ስንዴው ስንዴ ያፈራል፤ ገብሱም ገብስ ያፈራል እንጂ ስንዴው ገብስ ገብሱም ስንዴ ሆኖ አይገኝም። እንደዚሁም ወንጌልና ቁርዓን ተሰባጥረው ተጽፈው ቢቀርቡ (ቢሰበኩ) በምንም ተአምር ውሕደት ሊኖራቸው አይችልም። ይህም ማለት ቁርዓን ወንጌልን አይወክልም ወንጌልም ቁርዓንን አይተካም፣ ምክንያቱም ወንጌል የሚያስተምረው ሰማያዊ ፍልስፍና ነው ማለት የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የክርስቶስን አምላክነትና አዳኝነት ሲሆን ቁርዓን ግን የሚሰብከው ከዚህ የተለየ ነው ማለት "አላህ አይወርድም አይወልድም፣ ተጋሪ ቢጤ የለውም" የሚል ነው፤ ስለዚህ እነዚህ ሁለት እምነቶች ምንም አይነት ግንኙነት አይኖራቸውም።

ይህም ሆኖ ሁለቱ ወንድማማቾች ማለት ሙስሊሙና ክርስቲያኑ የየራሳቸውን እምነት ጠብቀው ተስማምተውና ተከባብረው እርስ በርስ እየተረዳዱ ለብዙ ዘመናት አብረው እንደመኖራቸው መጠን ያሳለፉትን ስፊና ረዥም ታሪካዊ ጉዞ ለታሪክ ጸሐፊዎች ልተወውና በቅርብ ጊዜ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በኅብረት የፈጸሙትን የማይረሳ ታሪካዊ ትዝታ ብቻ ባጭሩ ላስታውስ እወዳለሁ፣ በደርግ ዘመነ መንግሥት በታላቁ አንዋር መስጊድ አቅራቢያ የሚገኘው የቅዱስ ራጉኤል ቤተ ክርስቲያን ከስፍራው ተነስቶ ወደ እንጦጦ እንዲዛወር በተደረገው ያልተሳካ ሙከራ መርካቶ አዲስ ከተማ አካባቢ የሚኖረው ሙስሊሙና ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ ባለው ኃይል ባንድነት ተከላክሎ በሚያስደንቅ አኳኋን ሙከራውን አክሽፎ አስቀርቶታል።



ሁለተኛ በአፍሪካ አንደኛ በዓለም ሁለተኛ ነው እየተባለ የሚነገርለትን አዲስ ከተማ የሚገኘውን ባላራት ጉልላት የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ገንዘቡን አስተባብሮ ያሰራው ሙስሊሙና ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ መሆኑን ታሪክና ትውልድ ሲያስታውሱት ይኖራሉ። ስለዚህ የነ አህመድ ዲዳት ፓንፍሌት ስርጭት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያመጣል ብለን አንጠራጠርም።

በመልስ መጽሐፉ ላይ የጸሐፊው ምዕራፍና ንዑሳን ክፍሎች አልተለወጡም፤ በነበሩበት ተቀምጠዋል፤ አንዳንድ ንዑሳን ክፍሎች ተመሳሳይ በመሆናቸው በማጠጋጋት መልስ ሰጥቼባቸዋለሁ፣ የመልሱ አቀራረብ መጀመሪያ የደራሲውን ሙሉ ቃል ከጻፍሁ በኋላ እንደነገሩ ሁኔታ (እንደአስፈላጊነቱ) ባጭሩ ወይም በረዥሙ መልስ ተሰጥቶበታል፣ ሙሉ ቃሉን የጻፍሁበት ዋና ምክንያት አንባቢዎች መልሱን እያነበቡ ከፊተኛው ጋር እንዲያነፃጽሩት ይጠቅማል ብዬ ነው።

"ክርስቶስ በኢስላም" ለተሰኘው መጽሐፍ የመልሱ መጽሐፍ ስም "ክርስቶስን ከቁርዓን ጋር ምን አገናኘው?" (ቁርዓን ስለ ክርስቶስ ምን ያውቃል?) የሚል ስያሜ ሰጥቼዋለሁ።



www.ethiopianorthodox.org

## አንባቢው ልብ በል!

ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ
ያጠግባል ያረካል በቀላል ምሳሌ፤
ቀላቅለው ደባልቀው ቢዘሩት ሁዳዴ
ስንዴው ገብስ አይሆንም ገብሱ አይሆንም ስንዴ፤
ሁሉም ይበቅላሉ እንደዘራቸው እንደያገዳቸው
ፍሬም ያፈራሉ እንደያይነታቸው እንደጠባያቸው፤
ቀላቅለን ብንጽፈው ብንሰብከው ዘረን
ቁርዓን ወንጌል አይሆን ወንጌልም ቁርዓን፤
ቁርዓን ቁርዓን ነው ወንጌልም ወንጌል
አይቀላቀልም አይመሳሰልም ያ ቃል ከዚህ ቃል፤
በላይ በሰማይ ቤት የሚመሰክሩ
ሦስት አካላት ናቸው የማ.ተባበሩ፤
አብና ቃል መንፈስ ሳይነጣጠሉ
በላይ በሰማይ ቤት ይመሰክራሉ፤ 1 ዮሐ. 5 ቁ. 7-8
ቁርዓን በበኩሉ ይህን ይቃወማል
ዳኛው ምስክሩ ተጋሪ የሌለው አንድ አላህ ነው ይላል፤
አንድ አምላክ አይወርድም አይወልድም
በላይ ቤት በታች ቤት ቢጤ የለውም፤ 1-4 (ቁርዓን 112)



# አንደኛ ምዕራፍ

## የክርስቲያኖች ቅርበት

## ክርክር በቴሌቪዥን

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ጁን 5 ቀን 1983 ዓ.ም. እሁድ ዕለት "ኤስ. ኤ. ቢ. ሲ." (*SABC TV*) በመባል የሚታወቀው የቴሌቪዥን ድርጅት የመስቀል ጥያቄዎች በተሰኘ ፕሮግራም "ክርስትናና ኢስላም" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ሃይማኖታዊ ውይይት ለእይታ አብቅቶ ነበር፣ በውይይቱ ማብቂያ ላይ ዝግጅቱን በሊቀመንበርነት ያስተናገዱት ሚስተር ቢል ቻመርስ (*Bill Chamers*) የሚከተለውን አስተያየት ሰንዝረው ነበር "እንደማስበው ከሆነ ባሁኑ ጊዜ ለኢስላም መሥራች (ነቢዩ ሙሐመድ) በክርስቲያኑ ዘንድ ካላቸው ስፍራ ይልቅ የክርስትና መሥራች ኢየሱስ በሙስሊም ወገኖች ዘንድ ያላቸው ስፍራ በተወሰነ ደረጃ ላቅ ያለ እንደሆነ ይህን ውይይት መነሻ አድርጎ መናገር የሚቻል ይመስለኛል፤ የዚህ አወንታ ፋይዳ ምንድ ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ መሻቱን ለእናንተው ለተመልካቾች እንተወዋለን፤ ግና አንድ ጋር መወያየት መቻላችን በራሱ በጎ ነገር መሆኑን ሁላችሁም እንደምትስማሙበት እገምታለሁ" ብለዋል። ደራሲው በመቀጠል "ቢል" ታዳሚዎችን የሚጠሯቸው ያለምንም የመዓርግ ቅጥያ ነው፤ እጅግ በጣም አስደሳች ጠባይና ሥነ ምግባር የተላበሱ ቁርዓን በበጎነታቸው ከጠቀሳቸው ክርስቲያኖች አንዱ ናቸው ካለ በኋላ ለዚህም ማስረጃ የሚሆን ቁርዓን 5 ቁ. 82 ጠቅሶ "...እነዚያንም ክርስቲያኖች ነን ያሉትን ለነዚያ ለአመኑት (ለሙስሊሞች) በወዳጅነት በእርግጥ ይበልጥ የቀረቧቸው ሆነው ታገኛለህ፣ ይህም ከነሱ ውስጥ ቀሳውስትና መነኮሳት በመኖራቸውና እነሱም የማይኮሩ በመሆናቸው ነው" ብሏል።

www.ethiopianorthodox.org

**መልስ፣** ይህን የቴሌቪዥን ውይይት የጽሑፉ አዘጋጅ ያቀረበው እንደ መግቢያ አድርጎ ስለሆነ እኔም መልስ ልሰጥበት አልፈልግም፣ በርግጥ የመድረኩ ሰውዬ ቢል እንደተናገሩት ለውይይት መቀራረቡ ራሱ መልካም ጅምር ነው፣ በሁለቱ (በሙስሊሙና በክርስቲያኑ ምሑራን) መካከል በቅን ልቡና ላይ ተመሥርቶ ውይይቱ ቢቀጥል ይደገፍ ነበር፣ ይሁን እንጂ ባሁኑ ጊዜ የእስላም አክራሪዎች ሃይማኖቱን የመንግሥታቸው መመሪያ አድርገው ስለሚገለገሉበት ምኞት ብቻ ከመሆን አልፎ በተግባር ሊተረጎም የሚችል አይደለም።

## ኢየሱስና ደረጃው

"በውይይቱ የነበሩት ሙስሊሞች የኢየሱስን መዓርግ ከፍ አድርገው ሲያስተጋቡ ሌላውን ወገን ለማደናገር ወይም ለማስመሰል ሳይሆን አላህ በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ እንዲያስሙ ያዘዘውን ተመርኩዘው ነው፤ እንደ ሙስሊምነታቸው ይህን ከማድረግ ሌላ አማራጭ የላቸውም፣ ለዚህ ነው በተደጋጋሚ እንዲህ የሚሉት "እኛ ሙስሊሞች ኢየሱስ ከታላላቅ የአላህ መላክተኞች አንዱ መሆኑንና እርሱም ክርስቶስ እንደሆነ ያለምንም ተቃራኒ ፆታዎች ውሕደት ተአምራዊ በሆነ ሁኔታ እንደተወለደ (ይህን ግን የዘመናችን ክርስቲያኖች አይቀበሉትም) የሞተውን በአላህ ፈቃድ ሕያው እንዳደረገ ዓይነ ስውራንንና የሥጋ ደዌ ሕሙማንን በአላህ ፈቃድ እንደፈወሰ አምነን እንቀበላለን፣ በእርግጥም አንድ ሙስሊም የኢየሱስን ነቢይነት አምኖ ካልተቀበለ ሙስሊም ሊባል አይችልም" ብሏል።

**መልስ፣** ክርስቶስ እንደ ሌሎቹ ሰዎች ደረጃ መዳቢ አያስፈልገውም፣ ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ የሆነ የሰማይና የምድር ጌታ ነው። ሙስሊሞች ክብር የሰጣችሁት እየመሰላችሁ "ነቢይ፣ የእግዚአብሔር መላክተኛ፣ በድንግልና የተወለደ፣ ታላላቅ ተአምር ያደረገ ታላቅ ነው" እያላችሁ ታሞግሱታላችሁ፣ ይህ ሁሉ ከንቱ ውዳሴና ባዶ ቃላት ነው፣ በክርስቶስ ዘንድ ዋጋ የለውም፤ ክርስቶስ በምድር ላይ የቆየው 33 ዓመት ከሦስት ወራት ብቻ ነው፤ ሐዲስ



ኪዳንና ቁርዓን እንዳስረዱት የአብ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣውና ሥጋ የለበሰው ቀደም ሲል ነቢዩ ኢሳይያስ "የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድሆች የምስራችን (ወንጌልን) እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፣ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፣ ለተማረኩት ነፃነትን፣ ለታሰሩት መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል፣ የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት እሰብክ ዘንድ፣ የሚያለቅሱትንም አፅናና ዘንድ" ሲል በተናገረለት ትንቢት መሠረት ድውይ መፈወስ ሙት ማስነሳቱ፣ አጋንንት ማውጣቱ፣ ሞቶ መነሳቱና ወደሰማይ ማረጉ የአምላክነቱ መግለጫ ነው፤ ይህን ሐቅ ላለመቀበል የሚደረግ መከላከል ራስን ማታለልና የዋህነት ነው፣ ኢሳ. 61 ቁ. 1-3

## አስደሳች አጋጣሚ

ከሙቶ ዘጠና በላይ የሆኑት የክርክሩ ተሳታፊዎች ሳይደሰቱም ሳይገረሙም አልቀሩም፤ ምናልባት ጆሯቸውን ማመን ያልቻሉ አይጠፉም፤ የክርክሩ ይዘት ሙስሊሞች ከክርስቲያን ወንድሞቻቸው መልካም ስምን ለማትረፍ የሚያደርጉት ጥረት ነው የሚል አስተሳሰብ ሳይፈጠር አልቀረም ማለትም ሙስሊሞች ስለ ኢየሱስ ጥቂት መልካም ቃላት በመወርወር በምላሹ በአፃፉው ክርስቲያኖች ስለ ነቢዩ ሙሐመድ ጥቂት በጎ ቃላት እንዲናገሩላቸው በመሻት ያደረጉት "እከክልኝ ልከክልህ" ዓይነት ጨዋታ ሳይመስላቸው አልቀረም፣ ይህ ግን ቅሌት ወይም መናፍቅነት ነው ብሏል።

**መልስ፣** ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከማንም የመናፍቃን ጉባኤ ክብርና ምስጋና አይፈልግም፣ በሰማይ ዕልፍ አዕላፋት መላእክት፣ በምድር ደቂቀ አዳም ሌሊትና ቀን ያመሰግኑታል፣ እንደአምላክነቱ (እንደአዳኝነቱ) አምነን ብናከብረው ያከብረናል፣ ብንወደው ይወደናል፣ ብናስበው ያስበናል፣ ዋጋችንንም ይከፍለናል፣ እንደእግዚአብሔርነቱ ባናከብረው ግን በነፍስ በሥጋችን ይፈርድብናል፣ ይቀጣናል። ሃይማኖት "እንካ በእንካ" የሚተላለፍ ስጦታ አይደለም፣ ተመራምሮ አውቆ የሚድኑበት ረቂቅ መለኮታዊ

www.ethiopianorthodox.org

ፍልስፍና ነው በዓለም ፍጻሜ ዘመን ዋጋ ከፍሎ የሚያሰናብት የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

"የሰው ልጅ (ክርስቶስ) በምስጋና ክብሩ በመጣ ጊዜ ቅዱሳን መላእክት ከርሱ ጋራ ያን ጊዜ በምስጋናው ዙፋን ይቀመጣል፣ አሕዛብ ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፣ ጠባቂ በጎችን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፣ በጎችን በቀኙ ፍየሎችን በግራው ያቆማል፣ ያን ጊዜ ንጉሡ በቀኙ የቆሙትን ይላቸዋል፣ እናንተ የአባቴ ቡሩካን ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ትወረሱ ዘንድ ወደ እኔ ኑ፣ ... ከዚያ በኋላ ደግሞ በግራው የቆሙትን እናንተ ርጉማን ከእኔ ራቁ ሂዱ ወደ ዘላለም እሳት ለሰይጣንና ለመላክተኞቹ ወደተዘጋጀው ይላቸዋል" ማቴ. 25 ቁ. 31-41 ተመልከት።

## ሥር የሰደደ ጥላቻ

"ክርስቲያኖች ቢጠረጥሩን አይፈረድባቸውም፣ ለዘመናት የተካኑትና የሠለጠኑት በዚሁ መልክ ነውና፣ ይኸውም ሙሐመድንና ኢስላምን እንዲጠሉ በተቀነባበረ ፕሮግራም ውስጥ እንዲያልፉ ተደርገዋል፣ በዚህ ረገድ የዛሬ 150 ዓመት ገደማ ቶማስ ካርላይል ስለክርስቲያን ወንድሞቹ እንዲህ ብሏል "በመጥፎ ስሜት በመነሳሳት በዚህ ሰው (በነብዩ ሙሐመድ) ላይ የለጠፍናቸው ቅጥፈቶች የሚያሳዝኑ እኛኑ ነው፣ ቢሆንም ትክክለኛውን የኢስላም መልእክት ሳይረዱ በጥርጣሬና ባላዋቂነት ለሚኖሩት 1,200,000,000 ክርስቲያኖች በከፊል ተጠያቂ የምንሆነው እኛ ሙስሊሞች ነን፣ ክርስቲያኖች በኢስላም ላይ ያላቸውን የተሳሳተ አመለካከት ለመቀየር ያደረግነው ሁነኛ ጥረት የለም" ተብሏል።

<u>መልስ፣</u> እኛ ክርስቲያኖች በእስልምና ሃይማኖት ላይ እንኳን ሥር የሰደደ ጊዚያዊ ጥላቻ የለንም፣ ሙሐመድንና ሃይማኖቱንም እንድንጠላ የተቀነባበረ ፕሮግራም አልተላለፈልንም፣ የፈጠራ ወሬ ነው። የክርስቲያኖች መመሪያ ክርስቶስ ያስተማረው ወንጌልና ሐዋርያት የጻፏቸው መልዕክቶች ናቸው። ከነዚህ በየትኛው ክፍል



ውስጥ ነው የተቀነባበረው የጥላቻው ፕሮግራም የተላለፈው? ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተላለፈልን መመሪያ "እኔ ግን እላችኋለሁ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ የሚረግሟችሁን መርቁ፣ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፣ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ" የሚል ፍቅርንና ትሕትናን የተላበሰ ማህበራዊ ኑሮን የሚያስተምር ነው። ማቴ. 5 ቁ.44።

ትክክለኛውን ነገር ለማወቅ ከተፈለገ በክርስትናና በእስልምና ሃይማኖቶች መካከል የዓላማ ልዩነት ብቻ ሳይሆን የፍልስፍናም ልዩነት አለ፣ እኛ ክርስቲያኖች "እግዚአብሔር በስም ሦስት በመለኮት አንድ እግዚአብሔር ነው" እንላለን፤ ሙስሊሞች ግን "እግዚአብሔር አንድ ነው" ትላላችሁ፣ "ክርስቶስ አምላክ ነው ወረደ ተወለደ" ስንል፣ እናንተ ግን "ክርስቶስ ነቢይ ነው አምላክ አይወርድም አይወለድም" ትላላችሁ፣ ይህ ግዙፍ ልዩነት ነው፣ ይህም ግዙፍ ልዩነት የመጣው ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ከ600 ዓመት በኋላ ነው፣ ክርስቲያኖችስ እንዴት አላዋቂዎች ናቸው ይባላሉ? እግዚአብሔር ይቅር ይበላችሁ፣ አላዋቂዎችስ እናንተው ሙስሊሞች ናችሁ፣ ፍጡርና ፈጣሪን ለይታችሁ ባለማወቃችሁ፣ ተጠያቂዎችም የምትሆኑት በራሳችሁ እምነት እንጂ በክርስቲያኖች አምልኮት በከፊልም ሆነ በሙሉ ተጠያቂዎች እንደማትሆኑ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፤ ማንም ቢሆን የዘራውን ያጭዳል እንጂ ሌላው የዘራውን አያጭድም፣ ቶማስ ካርላይል እንዲህ ብሏል ክርስቲያኖች ሞኞች (አላዋቂዎች) ናቸው እያሉ የሌሎችን ነውር ነቀፋ ከማውራት ይልቅ አስቀድሞ የራስን ነውር ማስወገድ ያስፈልጋል፣ የኋላ ኋላ ከተጠያቂነት እንደማታመልጡ ከወዲሁ ተረድታችሁ ግንዛቤ በመውሰድ ራስን ማስተካከል ብልህነት ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "እትፍረዱ እንዳይፈረድባችሁ በሰፈራችሁበት ላይን በመዘናችሁበት ሚዛን ይሰፈርላችኋልና፣ ለምን በወንድምህ ዓይን ላይ ያለውን ስንጣቂ ታያለህ? በራስህ ዓይን ላይ ያለውን ምሰሶ ሳታይ እንዴትስ ከወንድምህ ዓይን ላይ ስንጣቂ ላውጣልህ ትለዋለህ? እነሆ ባንተ ዓይን



www.ethiopianorthodox.org

ላይ ስንጣቂ አለ፣ አንተ ግብዝ አስቀድመህ በራስህ ዓይን ላይ ያለውን ስንጣቂ አውጣ፤ ከዚያ በኋላ በባልንጀራህ ዓይን ላይ ያለውን ምስሶ ታወጣለታለህ፣ ላውጣልህ ትለዋለህ" ይላል ማቴ. 7 ቁ. 1-6 ተመልከት።

## የክርስትና ውቅያኖስ

ደቡብ አፍሪካ የክርስትና ውቅያኖስ ናት፣ ከአፍሪካ አህጉር ሊቢያ ከፍተኛ የሙስሊም ሕዝብ አኃዝ ስላላት የምትኮራ ከሆነ ደቡብ አፍሪካም ባላት የክርስቲያኖች ቁጥር ልትኮራ ይገባታል፣ በዚች የክርስትና ውቅያኖስ (ደቡብ አፍሪካ) የሙስሊሞች ቁጥር ከጠቅላላው ሕዝብ ሁለት ከመቶ ብቻ ነው፣ ድምጽ የለሽና አናሳ ነን፣ በቁጥር በምንም የማንገባ በፖለቲካው መድረክም ምንም ቦታ የሌለን ስንሆን በኢኮኖሚው መስክም ያጣን የነጣን ድሀ ነን፣ እንደ አፐን ሄመር ያለው ግለሰብ የመላውን ሙስሊም ንብረት ሊገዛ ይችላል፣ ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ለእንቅስቃሴ አይጋብዝም ብለን ብንቀመጥም ምናልባት ይቅርታ ይደረግልን ይሆናል፣ ግን በጭራሽ አናደርገውም ተወደደም ተጠላም የፈጣሪን ፍላጎት ማስተጋባትና እውነትን የማወጅ ግዴታ አለብን። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ "እውነትን ታውቃላችሁ፣ እውነትም አርነት ታወጣችኋለች" ብሏል ዮሐ. 8 ቁ. 32።

መልስ፣ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ የተናገረው ለዘመናት በተስፋ ይጠባበቁት የነበረው መሢሕ ክርስቶስ ራሱ መሆኑን አምነው ለተቀበሉት አይሁድ ደቀመዛሙርቱ መመሪያ እንዲሆናቸው ነው። ይህን ቃል ከመመሪያው (ከክርስትና ትምህርት) ውጭ የሆነ ኢአማኒ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል እያለ ለፈለገው ዲስኩር ማጣፈጫ ሊያደርገው አይችልም፤ ቃሉ በውነት ለውነት የቆመ ሰው ለማስረጃነት ቢጠቅሰው ባልከፋም ነበር። የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ ግን ለውነት ዓላማ የቆመ ባለመሆኑ ሊጠቀምበት አይገባም፣ ለውነት የቆመ ቢሆንማ የሊቢያን ሙስሊሞች መናሐሪያነት፣ የደቡብ አፍሪካን የክርስትና ውቅያኖስነት ሲመሰክር ኢትዮጵያም በምሥራቅ



አፍሪካን የክርስትና ውቅያኖስነት ሲመሰክር ኢትዮጵያም በምሥራቅ
አፍሪካ ብቸኛ የክርስትና ደሴት ሆና መኖሯን ሊመሰክር በተገባው ነበር፣ የክርስትናን ሕይወት በመቀበል ከደቡብ አፍሪካና ከኢትዮጵያ ማን ይቀድማል? ኢትዮጵያ ክርስትናን በመቀበል እንኳን ደቡብ አፍሪካ አውሮፓ አይቀድማትም፣ መጠቀስ የሚገባው መጠነ ስፋቱ ብቻ ሳይሆን ቀዳሚነትም መታሰብ ነበረበት፤ ይሁን እንጂ ጸሐፊው ይህ ሁሉ ዓላማው አልነበረምና አያስደንቅም።



www.ethiopianorthodox.org

በስም ብታቆላምጡት በቃላት ብትክቡት ብትልቡት አይጠቅማችሁም አትጠቅሙትም፤ የማርያም ልጅ የመሢሕ ክርስቶስ መውረድ መወለዱንና አዳኝነቱን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ እኩልነቱን አምናችሁ እስካልተቀበላችሁ ድረስ ዋጋ የላችሁም፤ "እነሆ የእግዚአብሔር በግ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ"፤ "ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ ከርሱ ጋራ የለም፣ በወልድ የሚያምን አብም ደግሞ ከርሱ ጋራ ነው" "በእኔ በኩል ካልሆነ በስተቀር ወደአብ ሊመጣ የሚችል የለም" ዮሐ. 1 ቁ. 29፣ 1ዮሐ. 2 ቁ. 23፣ ዮሐ. 6ቁ. 44፣ ማቴ. 16 ቁ. 16 ተመልከት።

## ኢሳ ወደ ኢየሱስ

ቅዱስ ቁርዓን ኢየሱስን የሚጠራው "ኢሳ" በማለት ነው። በእርግጥ ይህ ስም ገና ሲወለድ የተጠራበት በመሆኑ በብዙ ቦታ ተከትቦ እናገኘዋለን። "ኢሳ" በአረብኛ "ኤሳው" በእብራይስጥ ሲሆን ብሉያዊ (ጥንታዊ) አጠራሩ ደግሞ "የህሹ" ነበር። ይህም ጥንታዊ ስያሜ የምዕራቡ ሕዝበ ክርስቲያን ኢየሱስ በማለት ላቲናዊ ቃና እንዲኖረው አድርጎታል። ኢየሱስ (JESUS) በተሰኘው ስም ውስጥ የምናገኛቸው ሁለት ፊደሎች " J (ጅ) " እና ሁለተኛው " S (ኤስ) " በኦርጅናሉ በኢየሱስ ቋንቋ ውስጥ የሉም፣ በሴማዊ ቋንቋዎች ውስጥም አናገኛቸውም፤ ቃሉ ያለምንም ውጣ ውረድ ኤሳው (ESAU) ነው፣ ኤሳው የተለመደ የአይሁድ መጠሪያ ስም ነው። "ዘፍጥረት" በሚል መጠሪያ በሚታወቀው የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ መጽሐፍ ውስጥ ብቻ ከ30 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፣ በኢየሱስ ላይ የስቅላት ፍርድ ካሳለፈው ከአይሁድ ጉባኤ ሳንሂድሪን መካከል ቢያንስ አንድ "ኢየሱስ" (JESUS) የሚባል ሰው እንደነበረ ይታመናል። አይሁዳዊው የታሪክ ሊቅ ጆሲፈስ "ቡክ ኦፍ አንቲኪውቲስ" በተሰኘው መጽሐፉ 25 ኢየሱስ ተብለው የሚጠሩ ሰዎችን ጠቅሷል። አዲስ ኪዳን በርያሱስ (BAR-JESUS) ስለተባለ ጠንቋይና ሐሰተኛ ነቢይ አውግቷል የሐዋ. ሥራ 13 ቁ. 6



ኢዮስጦስ የተባለ (JESUS-JUSTUS) የጳውሎስ ዘመነኛ የሆነ ሚሲዮናዊ ክርስቲያንም እንደነበረ በቆላስይስ 4 ቁ. 11 ተጠቅሷል። በእርግጥ እነኚህ ሰዎች ከመርየም ልጅ ኢሳ የተለዩ ማለትም ሞክሼዎች ብቻ ነበሩ። ኤሳው (ESAU) የሚለውን መጠሪያ ወደ ኢየሱስ (JESUS) በመቀየር አዲስ ስም ተፈጠረ። ክርስቶስ ካረገ ከሁለት ዓመት በኋላ ይህ እንግዳ ስም ኢየሱስ የልጆቻቸው መጠሪያ ስም እንዲሆን አይሁዳውያንም ሆኑ ክርስቲያኖች ፈቃደኞች አልነበሩም፣ ምክንያቱም አይሁዳውያኑ ኢየሱስ የነርሱን እምነት ያልተቀበለ በመሆኑ ስሙን እንኳ መስማት የሚቀፋቸው ሆኑ፣ ክርስቲያኖች ደግሞ የአምላካቸው መጠሪያ በመሆኑ ይህን መለኮታዊ ስም ለሰብአዊ ፍጡር ሊያጋሩት አልፈለጉም። ሙስሊሞች ግን ልጆቻቸውን ኢሳ ብለው ለመሰየም አያቅማሙም፣ ምክንያቱም ይህ ስም ያንድ ክቡር የአላህ ባሪያና አገልጋይ መጠሪያ በመሆኑ ነው ብሏል።

__መልስ፣__ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ኤሳው ከተባለው ስም ኢየሱስ የተባለው እንግዳ ስም ተፈጠረ ሲል በኢየሱስ ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ ከፍቷል፣ ዘመቻው ሙስሊሙን አይጠቅምም፣ ክርስቲያኑንም አይጎዳም። ኢየሱስ የተባለው ስም ሰው-ሠራሽ አይደለም። ከሣቴ ቅዱስ (ሥላሴ) አንዱ የማርያም ልጅ በፊደል ፎርሙላ ስም አልወጣለትም፤ መልቲው ጸሐፊ "ኢየሱስ" ገና ሲወለድ የተጠራበት ስም ነው ብሏል፣ ቅጠፈት ነው ወይም አለማወቅ ነው፤ ገና ከመፀነሱ በፊት ነው የወጣለት፣ ከመፀነሱ በፊት ቅዱስ ገብርኤል "ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ብለሽ ትጠሪዋለሽ" በማለት ስሙን ከነትርጓሜው ነግሯታል። ኢየሱስ ማለት "መድኃኒት" ማለት ነው። ማቴ. 1ቁ.21፣ ሉቃ. 1 ቁ.31፣ 2 ቁ.21።

"በርካታ ማስገንዘቢያዎች" የሚለው በመጨረሻዎቹ ገፆች መልስ ተሰጥቶበታልና በዚያው ይመልከቱ።



www.ethiopianorthodox.org

# ሦስተኛ ምዕራፍ

## የማርያም መወለድ (መለኮታዊ ራዕይ)

ታሪኩ እንዲህ ነው፤ የኢየሱስ ሴት አያት የመርየም እናት ሐና መሀን ነበረች፤ አላህ (ሱ.ወ.) ልጅ ይሰጣት ዘንድ ከልቧ መማጠን ጀመረች፤ ልጅ ከተቸረችም የቤተመቅደስ አገልጋይ እንደምታደርገው ተሳለች፣ አላህም ልመናዋን ተቀበላትና መርየም ተወለደች፣ ሐና የተመኘችው ወንድ ልጅ ስለነበረ በተወለደችው ልጅ እምብዛም አልፈነደቀችም፣ ራሷ ለተሳለችው አገልግሎት ሴት ልጅ እንደ ወንድ ልጅ ብቁ ልትሆን እንደማትችል ተሰማት፤ ታዲያ ምን ታድርግ? ስዕለት አለባት፣ የነቡራት አማራጭ መርየም እስክታድግና ራሷን እስክትችል መጠበቅ ነበር፣ ጊዜው ደረሰ፣ ሐና የምታንን ልጇን ወደ ቤተ መቅደስ ወሰደቻት፣ እንድታገለግልም አስረከበቻት፣ እያንዳንዱ መምህር ለዚች ተወዳጅ ልጅ የነፍስ አባት ለመሆን ቋመጠ፣ በመካከላቸው ጭቅጭቅ ተፈጠረ፣ ዕጣም ተጣጣሉ፣ ዘካርያስ ከብዙ ውዝግብ በኋላ ባለዕድል ሆነ ተብሏል፤

<u>መልስ፣</u> ባለታሪኩ ይናገር፣ መለኮታዊ ራዕይ የሚለው በዚሁ ተጠቃሏል። የድንግል ማርያም እናት ሐና አባቷ ኢያቄም ይባላሉ፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ደጋግ ሰዎች ነበሩ፣ እግዚአብሔር የተባረከ ልጅ እንዲሰጣቸው ይለምኑት ነበር። ልጅ ከተወለደ ወንድም ይሁን ሴት ለእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሚያደርጉት ተሳሉ፣ ስዕለታቸው ሰምሮ ድንግል ማርያም ተወለደች፣ ሦስት ዓመት ሲሆናት እናትና አባቷ ወስደው ለካህናት ሰጧት፣ ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ ይባላል። ዘካርያስ ሕዝቡን በደወል ሰብስቦ ስለኑሮዋ ሲመካከሩ የእግዚአብሔር መልአክ ሰማያዊ መና ሰማያዊ ጽዋ ይዞ በአየር ላይ ታየ፣ ለሕፃኗ የወረደ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ይሆናል በማለት ትተዋት ፈቀቅ ሲሉ መልአኩ ወደርሷ ወርዶ መግቧት ወደመጣበት ተመለሰ፣ ካህናቱም የምግቧ ነገር ከተያዘልን ችግር የለም በማለት ወደ ቤተ መቅደስ አስገብተው አስቀመጧት፤ ቅድስት ንጽሕት ድንግል ማርያም ከእናትና ከአባቷ ተለይታ ቅዱሳን መላዕክት እያጫወቷትና እያረጋጓት በቤተ መቅደስ 12 ዓመት ተቀመጠች፣ ከእናት ከአባቷ ጋር የቆየችው 3 ዓመት በድምሩ 15 ዓመት ሲሆናት ቅዱስ ገብርኤል ወደርሷ ቀርቦ "ፀጋን የተሞላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና፣ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ" አላት፣ እርሷም ከነገሩ የተነሳ ደነገጠችና ይህ ዓይነቱ ሰላምታ ምንድነው? በማለት አሰበች፣ መልአኩም ማርያም ሆይ! አትፍሪ ከእግዚአብሔር ዘንድ ፀጋን አግኝ ተሻልና፣ እነሆም ትፀንሻለሽ፣ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፣ ስሙንም ኢየሱስ ብለሽ ትጠሪዋለሽ፣ ይህ ታላቅ ይሆናል፣ የልዑል ልጅም ይባላል፣ እግዚአብሔር አምላክም ያባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፣ በያዕቆብ ወገን ላይ ለዘላለም ይነግሣል፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም አላት፣ ማርያምም ወንድ ሳላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል አለችው፣ መልአኩም መንፈስ ቅዱስ ወደ አንቺ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጋርድሻል፣ ስለዚህ ቅዱሱ ካንቺ የተወለደው የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፤ እነኋት ዘመድሽ ኤልሳቤጥ በእርጅናዋ ጊዜ ልጅ ፀንሳለች፣ ይህም ወር ስድስተኛዋ ነው ለዚያች መካን ለምትባለው፤ ማርያምም እነሆኝ የእግዚአብሔር ባሪያ እንደቃልህ ይደረግልኝ አለችው፣ ወዲያው ከሦስቱ አንዱ እግዚአብሔር ወልድ (የአብ ቃል) በማሕፀኗ አደረ።

በዚያ ወራት ማርያም ፈጥና ተነስታ ወደ ሊባኖስ ተራራ ሄደች፣ ወደ ዘካርያስም ቤት ገብታ ለኤልሳቤጥ ሰላምታ ሰጠቻት፣ ኤልሳቤጥ የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በሆዷ ዘለለ፣ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ መላባት፣ በታላቅ ድምፅም እንዲህ ስትል ጮኸች፣ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ፣ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፣ የጌታዬ እናቱ ወደ እኔ ትመጭ ዘንድ ይገባልን? እነሆ! ሰላምታሽን በሰማሁ ጊዜ ፅንሱ በሆዴ በደስታ ዘሏልና።

ማርያም አለች "ነፍሴ እግዚአብሔርን ታላቅ ታደርገዋለች፣ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ደስ ይላታል፣ የባሪያውን መዋረድ አይቷልና፣ <u>እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል</u>፣ እርሱ ብርቱ የሚሆን ታላቅ ሥራ በእኔ ላይ አድርጓልና፣ ስሙ ቅዱስ ነው" ይላል፤ ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ይህ ነው፣


www.ethiopianorthodox.org

ድንግል ማርያምን ከእናቷ ማሕፀን ጀምሮ ከሴቶች ሁሉ ለይቶ የመረጣት እግዚአብሔር ነው፤ ስለመመረጧ ምሥራቹንም የነገራት ቅዱስ ገብርኤል ነው። ቅዱስ ገብርኤል "ፀጋን የተመላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና፣ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ፣ የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው" ሲል ሰማያዊ ምሥራቹን ነግሯታል፤ ከ600 ዓ.ም. በኋላ የተነሳው ሙሐመድ ደግሞ የቅዱስ ገብርኤልን ቃል በመኮረጅ "ከሴቶች ሁሉ የተመረጠች ናት" በማለት ቆንጽሎ ተናግሮታል፤ የትኛው አነጋገር ይበልጣል? የትኛውስ አገላለጥ ርካታ ይሰጣል? አንባቢው ይፍረድ፤

ድንግል ማርያምም "ፀጋን የተመላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ" የሚለውን ቃል ሰምታ ክርስቶስን ፀንሳ ሳለች "ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል" ስትል በተናገረችው መሠረት ክርስቲያኖች "እናታችን እመቤታችን አማላጃችንና መመኪያችን ድንግል ማርያም ናት" እያሉ ያከብሯታል፣ ያገኗታል፣ ያመሰግኗታል፤ ድንግል ማርያምም በተሰጣት ቃል ኪዳን መሠረት ከልጇ ከወዳጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ታማልዳቸዋለች፣ ከክፉ ነገር ትጠብቃቸዋለች፣ ረድኤቷን በረከቷን ታድላቸዋለች።

## ሣራና አጋር

"አይሁዳውያን ዓይን ያወጣ ዘረኛነትን የተማሩት ከመጽሐፍ ቅዱሳቸው ነው፣ በመጽሐፋቸው እንደተናገሩት አብርሃም ሁለት ሚስቶች (ሣራና አጋር) ነበሩት፤ እኛ "ከአብርሃም ሕጋዊ ሚስት ከሣራ የተገኘን የአብርሃም ልጆች ስንሆን ዓረቦች ግን ከባሪያይቱ ከአጋር የተገኙ በመሆናቸው አጥንተ ሰባራ ዝቅተኞች ናቸው" ይላሉ አይሁዳውያን፤ ታዲያ ቁርዓንን የደረሰው (ፈጥሮ የጻፈው) ሙሐመድ ነው የሚሉ ሰዎች ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ዓረብ ሆነው ሳለ (ነገሩ በርግጥ እንደሚሉት ከሆነ) ለአይሁዳዊቷ ማርያም ከፍተኛ መዓርግ



መስጠታቸው ለምን እንደሆነ ሊገልጡልን ይችላሉ? መልሱ ቀላል ነው፤ ምርጫ አልነበራቸውም፤ የግላቸውን ፍላጎትና አሳብ በቁርዓን ምንባቦች ላይ የማስፈር መብትም ሆነ ሥልጣን አልነበራቸውም፣ እርሱ (ንግግሩ) የሚወርድ ራዕይ እንጂ ሌላ አልነበረም"፣ ቅዱስ ቁርዓን 53 ቁ.4።

<u>መልስ፣</u> መጽሐፍ ቅዱስ የአይሁድ መጽሐፍ ብቻ አይደለም፣ በሰዎች ፍላጎትም የተጻፈ አይደለም፣ እግዚአብሔር በገለጣቸው በቅዱሳን አባቶች አዘጋጅነት የተጻፈ የታሪክ የሃይማኖትና የፍልስፍና መዝገብ ነው፣ 2ኛ ጴጥ. 1 ቁ. 21፣ ከዚህ የተነሳ መጽሐፍ ቅዱስን በመላው ዓለም የሚኖሩት አይሁዶችና ክርስቲያኖች የሃይማኖታቸው መመሪያ (የእግዚአብሔር ሕገ መንግሥት) አድርገው ተቀብለውታል። መጽሐፍ ቅዱስ የማይዳስሰው ታሪክ ባይኖርም ያለምክንያት የሴትና የወንድ ታሪክ ተሰባጥሮ አይጻፍም፤ የሴቶች ታሪክ የሚጻፈው ከባሎቻቸው ጋር ወይም ልዩ ምክንያት ሲኖራቸው ነው።

የሣራና የአጋር ታሪክ ሊጻፍ የቻለው ከአብርሃም ታሪክ ጋር ነው። ሣራ የአብርሃም ሕጋዊት ሚስቱ ስትሆን አጋር ደግሞ ገረዱ መሆኗ በብሉይ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በአዲስ ኪዳንም ተጠቅሷል፤ በተለይ የገረዲቱ የአጋር ታሪክ የተጻፈበት ልዩ ምክንያት ነበረው።

እመቤቷ ሣራ ልጅ ስላልነበራት አብርሃም ከአጋር ልጅ እንዲወልድ ሣራ ፈቀደችለት፣ አጋር ግን መፅነሷን ስታረጋግጥ እመቤቷን መናቅ ማቃለል ጀመረች፤ እግዚአብሔርም መናቋን ተመልክቶ ሣራን አሰባት፣ ወንድ ልጅ ይስሐቅን ሰጣት፣ ሣራ ከአጋር የተወለደው እስማኤል ከልጇ ከይስሐቅ ጋር ሲጫወት አይታ የዚች ባሪያ ልጅ ከልጇ ጋር ሊወርስ አይገባውም በማለት ፊት ነሳቻት፣ ተበቀለቻት፣ በዚህ ምክንያት አጋር ልጇን ይዛ ወደ ምድረ በዳ ተሰደደች፣ እግዚአብሔር ግን አልተለያትም፣ የምትበላውና የምትጠጣው አላሳጣትም፣ ልጇም እስማኤል የምድረ በዳ አዳኝ ቀስተኛ ሆኖ አደገ።



www.ethiopianorthodox.org

ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነስቶ ከተወለደና ሰው ከሆነ በኋላ "ወረደ ተወለደ ተጠመቀ ተሰቀለ ሞተ ተነሳ ዓረገ ባባቱ ቀኝ ተቀመጠ" የሚለው የሐዲስ ኪዳንና የሐዋርያት ታሪክ በሙሉ የክርስቶስና የድንግል ማርያም ታሪክ ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያን ሁሉ መከራ የተቀበለው ከድንግል ማርያም በለበሰው ሥጋ ነው እንጂ በመለኮቱማ ዘላለማዊ አምላክ ነው። 1ኛ ጴጥ. 3 ቁ. 19።

በተለይ ሐዲስ ኪዳን የተጻፈው የክርስቶስን ታሪክ ባጭሩ ለማስታወስ ነው፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ ሁሉ የሠራው ሥራ ያስተማረው ትምህርት በሙሉ ቢጻፍ ኖሮ ሰማይና ምድር ብራና (ወረቀት) ወንዞችና ባሕሮች ቀለም፣ እንጨቶችና ሣሮች ብዕር፣ ሰዎችና መላእክት ጸሐፊዎች ቢሆኑ ጽፈው ባልፈጸሙትም ነበር፣ ዮሐ. 21 ቁ. 25፤ "ኢየሱስ ብዙ ሌላ ተአምራት አደረገ በደቀመዛሙርቱ ፊት በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ፣ ባመናችሁም ጊዜ በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ለምልክት ተጻፈ" ዮሐ. 20 ቁ. 30፤

ባታውቁት ነው እንጂ ከዚህም ሌላ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ያልተጠቀሱ እግዚአብሔር የገለጠላቸው ቅዱሳን አባቶች በእናቱ በድንግል ማርያምና በክርስቶስ ስም የጻፉቸው በቤተ ክርስቲያናችን ዘወትር የሚነበቡና የሚጸለዩባቸው ቁጥር ስፍር የሌላቸው ልዩ ልዩ መጻሕፍት አሉ፣ "በጠባብ ኩሬ ውስጥ የምትኖር ዕንቁራሪት ሌላ ሰፊ ውቂያኖስ ያለ አይመስላትም" ይባል የለም?



## አራተኛ ምዕራፍ

### የምሥራች

"መላእክት ያሉትን (አስታውስ) መርየም ሆይ! አላህ ከርሱ በሆነው ቃል ስሙ አልመሲሕ ኢሳ የመርየም ልጅ በዚህ ዓለምና በመጨረሻው ዓለም የተከበረ ከባለሟሎቹም በሆነ (ልጅ) ያበስርሻል" ቁርዓን 3 ቁ. 45።

ከተጠቀሰው አንቀጽ የምንረዳው ኢየሱስ አልመሲሕ ለማርያም የተላከ "የአላህ የሁን ቃል" መሆኑን ነው፤ ነገር ግን ክርስቲያኖች ይህን አንቀጽ የተረዱት ያለአግባብ ነው። ኢየሱስ (ኢሳ) የሚለውን ስም ከሥጋዊ አምላክ እሳቤ ጋር ሲያይዙት "ከርሱ በሆነው ቃል" የሚለውን ሐረግ ደግሞ አምላክ ማለት ነው ይላሉ፣ (ይህ ስህተት ነው) ተብሏል።

<u>መልስ፣</u> እኛ ክርስቲያኖች አልተሳሳትንም፣ የተሳሳታችሁት እናንተው ሙስሊሞች ናችሁ፣ ቁርዓናችሁ "አልመሲሕ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማርያም የተላከ የአላህ የሁን ቃል ነው" ይላል፣ ይህን ቃል በትክክል አንብቦ መተርጎም ተስኗችሁ ወይም አልዋጥላችሁ ብሎ አድበስብሳችሁ ታልፉታላችሁ፣ "የአላህ የሁን ቃል" ማለት "ሥጋ የሆነ ቃል" ማለት ነው፣ ሥጋ የሆነ ቃል ማለትም ሥጋ የለበሰ ሰው የሆነ አምላክ ማለት ነው። የሙስሊሞች ታላቁ ችግራችሁ "የቃል ሥጋ መሆን" ምሥጢር ተሰውሮባችሁ መኖራችሁ ነው፣ እግዚአብሔር ይግለጥላችሁ፣ ማመዛዘኛ አእምሮ ይስጣችሁ እያልን እንጸልይላችኋለን።

ከላይ አንብባችሁ በደፈናው የምታልፉትን "የሁን ቃል" "የቃል ሥጋ ሆን" ትርጓሜ እስልምና ከመመሥረቱ ከ600 ዓ.ም. በፊት የነበረው የምሥጢረ ሥጋዌ መሐንዲስ ታላቁ ወንጌላዊው ዮሐንስ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት የጻፈውን ግልጥ ማስረጃ ሙሉ ቃል እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉም ተሰበሰቡ፣ ተደነቁም ፣ እያንዳንዱ ሰው በቋንቋው ሲናገሩ ይሰማቸው ነበር፣ ሁሉም ደነገጡ ተደነቁም፣ እርስ በርሳቸው እንዲህ ሲሉ እነዚህ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እንዴት እኛ እያንዳንዳችን በተወለድንበት ቋንቋ ሲናገሩ እንሰማቸዋለን? ......እግዚአብሔር ይላል በኋላ ጊዜ ሥጋ በለበሱ ሁሉ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ፣ ወንዶችም ሴቶችም ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፣ ጎበዛዝቶቻችሁም ራዕይ ያያሉ፣ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፣ በዚያች ወራት በወንዶችም በሴቶችም ባሮቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፣ ትንቢት ይናገራሉ" ይላል፣ የሐዋ. ሥራ 2 ቁ.1-18፣ ኢዩኤል 3 ቁ. 1 ተመልከት።

እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደተገለጠው መደበኞቹ 120 የክርስቶስ ቤተሰቦች (ሐዋርያት) መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው መንፈሳዊ ኃይል ተላብሰዋል፣ ከእርጅና ታድሰዋል፣ በአእምሮ ጎልምሰዋል፣ አንድ ቋንቋ ብቻ ያውቁ የነበሩት 71 ቋንቋ ተጨምሮላቸዋል፣ ፈሪዎች የነበሩት ደፋሮች ሆነዋል፤ በዚህ ዓይነት ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ እየረዳቸው የወንጌልን ትምህርት ባጭር ጊዜ ውስጥ በመላው ዓለም ሊያዳርሱ ችለዋል፣ "ቃላቸው (ድምፃቸው) ያልተሰማበት ስፍራ የለም፣ ንግግራቸውም በምድር ሁሉ ላይ ወጣ፣ ስብከታቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ደረሰ" በማለት ቀደም ሲል ነቢዩ ዳዊት የተናገረው ትንቢት በሐዋርያት ስብከት ተግባራዊ ሆኗል፣ መዝ. 19 ቁ. 3፣ ማር. 16 ቁ. 20።

የክርስትና ሃይማኖት በዚህ ዓይነት የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ርዳታ ተመሥርቶ 2000 ዓመታት ያህል እያስቆጠረ ነው፣ ወደፊትም በመንፈስ ቅዱስ ጠባቂነት እስከ ዓለም ፍጻሜ ይኖራል፣ ከ1400 ዘመን በላይ ያስቆጠረው እስልምና በቁርዓኑ ውስጥ ያልተጠቀሰ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ያልተነገረና የሌለ ከጊዜ በኋላ የፈጠራ ትንቢት እየጨመሩ ኅብረተሰብን ማወናበድ እግዚአብሔር ይወደዋልን? ይህ ዓይነቱ ፈጠራስ ለሙሐመድ ምን ይጠቅመዋል? ምንስ ክብር ይጨምርለታል? በስም የተጣበቀ ጥርስ ቢበሉበት አያደቅም፣ ቢስቁበት አያደምቅም እንደተባለው ነው፤



የክርስትና ሕይወት መሠረቱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ቃል ነው፣ "ነገሬን የሚሰማ የሚያደርገውም ቤቱን በጭንጫ ላይ የሠራ ብልህ ሰውን ይመስላል፣ ዝናም ዘነመ፣ ጎርፍ ጎረፈ፣ ነፋስም ነፈሰ፣ ያን ቤት ገፋው፣ አልወደቀም፣ በጭንጫ ላይ ተመሥርቷልና" ማቴ. 7 ቁ. 24፣

"እንደተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር ጸጋ መሠረት አስቀመጥሁ፣ እንደብልሃተኛ አናጺ ሌላውም በላዩ ይሠራል፣ ነገር ግን ሁሉ እያንዳንዱ ያስተውል፣ እንዴት በላዩ ይሠራ ዘንድ፣ ማንም አይችልምና ሌላ መሠረት ይመሠርት ዘንድ፣ ከዚያ ከተመሠረተው በቀር፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው"፣ 1 ቆሮ. 3 ቁ. 10፣ ማቴ. 21 ቁ. 42፣ መዝ. 118 ቁ. 22 : ;

## "እማዬ" ወይስ "አንች ሴት"

በዮሐንስ ወንጌል 2 ቁ. 4 እንደተጻፈው በቃና በተደረገው ሠርግ ኢየሱስ እናቱን እንዳመናጨቃት ይነበባል፣ እንዴት? አዎ! "አንች ሴት" አላት፣ "በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ "ካንች ጋር ምን አለኝ?"...... ባንችና በእኔ መካከል ምን ግንኙነት አለ?.....ምን አደርግልሻለሁ ...... አላት፣ ይህች "ሴት" ለዘጠኝ ወራት በማሕፀኗ የተሸከመችውና ምናልባትም ለሁለት ዓመታት ያጠባችው መሆኗን ዘንግቶት ይሆን? በርሱ የተነሳስ ለውግዘትና ለችግር የተዳረገች መሆኗን አልተገነዘበም? ለመሆኑ በሚናገረው ቋንቋ "እማዬ" የሚል ቃል የለምን? ነገሩ የሚያደንቅ ነው፣

ወንጌላውያን የመምህራቸውን ሰው አክባሪነት ትዕግስትና መከራ ተቀባይነቱን አጋነው ይሰብካሉ፣ "የሰላም ንጉሥም" እያሉ ያዜሙለታል፣

መልስ፣ ኢየሱስ እናቱን "አንች ሴት" በማለት አመናጭቋል ተብሏል፣ እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ ይባላል፣

www.ethiopianorthodox.org

# ጥብቅና ለኢየሱስ

በነቢዩ ሙሐመድ ላይ የተወረደው ቁርዓን ኢየሱስን ከባላንጣዎቹ የሐሰት ወሬና የስም ማጥፋት ዘመቻ ነፃ አድርጎታል፣ "ለእናቴ ታዛዥ አድርጎኛል፣ ትዕቢተኛ እምቢተኛም አላደረገኝም"፣ ቁርዓን 19 ቁ. 32፣

አላህ መርየምን መልካም ልጅ እንደምትወልድ (ቁርዓን 3 ቁ. 46) ሲያበስራት የሰጠችው መልስ "ጌታዬ ሆይ! ሰው ያልነካኝ ስሆን ለእኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል? አለች፤ ነገሩ እንደዚህ ነው፣ አላህ የሚሻውን ይፈጥራል፣ አንዳችን በሻ ጊዜ ለርሱ ሁን ይለዋል፣ ወዲያውኑም ይሆናል አላት፣ ጽሕፈትንም ጥበብንም ተውራትንና እንጅልንም ያስተምረዋል" ብሏል፣ ቁርዓን 3 ቁ. 47-48።

<u>መልስ</u>፣ ቁርዓን ኢየሱስን ከባላንጣዎቹ የሐሰት ወሬና የስም ማጥፋት ዘመቻ ነፃ አድርጎታል የተባለው ተራ ወሬ ነው፣ ቁርዓን ከክርስቶስ ልደት ከ600 ዓ.ም. በኋላ ተነስቶ ከየትኛው የስም ማጥፋት ዘመቻ ነው ነፃ ያደረገው? ከአባቴ በፊት ተወልጄ አባቴን አገለግለው ነበር እንደማለት ነው፣ ባላንጣዎቹ ናቸው የተባሉት አይሁድም ቢሆኑ የስም ማጥፋት ዘመቻ አላካሄዱበትም፣ አምላካችሁ መድኃኒታችሁ ነኝ ቢላቸው ጠልተው ተመቅኝተው ሰቅለው ገድለውታል፣ በክርስቶስና በአይሁድ መካከል ከዚህ ውጭ ሌላ ታሪክ አልነበረም፣ የሐሰት ወሬና የስም ማጥፋቱን ዘመቻ በሰፊው የከፈታችሁበት ዓለም ያወቃችሁ ባላንጣዎቹ እናንተው የሙስሊሙ አፈቀላጤዎች ናችሁ፣ ለምሳሌ ያህል ክርስቶስ አምላክ አይደለም፣ አምላክ አይወርድም አይወለድም ማለታችሁ፥ ስለክርስቶስ የተነገረውን ትንቢት ነጥቆ ለሙሐመድ መስጠታችሁ፥ አጽናኝ (ጰራቅሊጦስ) የተባለው ሙሐመድ ነው ማለታችሁ...... ይህን የመሳሰለውን ይፋዊ የጠላትነት ዘመቻ መጥቀስ ይቻላል።

ስለዚህ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ጥብቅና ሊቆምለት የማይፈልግ አይሁድ ጠላቶቹን በሕግ ተሟግቶ የረታና ያሸነፈ አምላክነቱን በሥራ የገለጠ የባሕርይ አምላክ ነው፣ ለዚህ አምላካዊ ባሕርዩ ማስረጃዎቹ፣ አብና መንፈስ ቅዱስ ሥራውና ደቀመዛሙርቱ ሐዋርያት ናቸው፣ "እኔና አብ አንድ ነን" "የሚያፅና ጰራቅሊጦስ በመጣ ጊዜ ከአብ ዘንድ ለእናንተ እኔ የምልከው የእውነት መንፈስ ከአብ የሚወጣ እርሱ ስለእኔ ይመሰክራል፣ እናንተ ደግሞ ትመሰክራላችሁ፣ ከጥንት ከእኔ ጋር ነበራችሁና፣ በእኔ እመኑ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ፣ በእኔ ባታምኑ በሥራዬ እመኑ" ዮሐ. 10 ቁ. 30-38።

www.ethiopianorthodox.org

<u>መልስ</u>፣ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ በጆሐንስበርግ ባይብል ሐውስ ከቄሱ ጋር ባደረገው ቆይታ የቁርዓንን ተወዳጅነትና የበላይነት የቄሱን ደካማነትና የራሱን ንፅፅራዊ (ኢስላማዊ) ተልዕኮ ከማንፀባርቅ በስተቀር ለመልስ የሚጋብዝ ቁምነገር አላገኘሁበትም፣ ወደ መጨረሻው ገደማ "አንድ ክርስቲያን ስለኢየሱስ መስማት የሚፈልገውን ሁሉ በቁርዓን ውስጥ ያገኛል፣ ያውም በላቀ ደረጃ ይላል፣ ጸሐፊው የላቀ ደረጃ የሚለው የትኛው ነው? ፍጡሩን ሙሐመድን ከፈጣሪው ከክርስቶስ ጋር እያወዳደረና እያበላለጠ ማቅረቡ ነውን? ስህተት ነው፣ ክርስቶስ እኮ ከሰማይ የወረደ ሰማያዊ አምላክ ነው፣ ሙሐመድ ግን ከምድር የተገኘ ምድራዊ ፍጡር ነው፣ ክርስቶስ እኮ ሞትን ድል አድርጎ የተነሳ ኃያል አምላክ ነው፣ ሙሐመድ ግን ፍጡር እንደመሆኑ መጠን የመጨረሻውን ትንሣኤ ይጠብቃል እንጂ ሞቶ አልተነሳም።

"ኢየሱስ ደግሞ አላቸው፣ "እኔ እሄዳለሁ፣ ትሹኛላችሁም በኃጢአታችሁም ትሞታላችሁ፣ እኔ ወደምሄድበት እናንተ ትመጡ ዘንድ አትችሉምና"፣ አይሁድም አሉ "እርሱ ራሱን ይገላል? እኔ ወደምሄድበት እናንተ መምጣት አትችሉም ማለቱ፣ አላቸውም "እናንተ ከታች እኔም ከላይ ነኝ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፣ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም" ሲል ሰማያዊ አምላክ መሆኑን በራሱ አንደበት አረጋግጦ መስክሯል፣ ዮሐ. 8 ቁ. 21-23።

## <u>ሰማይና ምድር</u>

ፅንፈኛው ክርስቲያን እንኳ ከላይ ከተዘረዘሩት እውነታዎች አንዲትን ቃል ወይም ንግግር ወደጎን ሊገፋ አይችልም፣ ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱሳዊውና በቁርዓናዊው ትረካዎች መካከል ያለው ልዩነት የሰማይና የምድር ያህል ነው፣ "ለእኔ ሁለቱም አንድ ናቸው፣ ምንድነው ልዩነታቸው?" አሉኝ ቄሱ፣ በመሠረቱ እነዚህ ትረካዎች በዝርዝራቸው ይስማማሉ፣ ነገር ግን በቅርበትና በጥልቅ



ስንመረምራቸው በመካከላቸው ያለው ልዩነት ግዙፍ መሆኑን እንገነዘባለን አልኳቸው፤

እስቲ አሁን በቅዱስ ቁርዓን 3 ቁ. 47 ላይ የተበሰረውን ተአምራዊ እርግዝና መጽሐፍ ቅዱስ ከሚለው ጋር ያነፃፅሩ፣ "የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት እንዲህ ነበር፣ እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች"፣ ማቴ. 1 ቁ 18፣ ከላይ የተጠቀሰው ቁርዓን ደግሞ "ጌታዬ ሆይ! ሰው ያልነካኝ ስሆን ለእኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል? አለች" እነዚህ ሐረጎች በፍሬ ነገራቸው ወንድ ስለማላውቅ" እና "ሰው ያልነካኝ ሲሆን" የሚሉት ምንም ልዩነት የላቸውም፣ ሁለቱ ጥቅሶች ተመሳሳይ ትርጉም ይሰጡናል፣ ነገር ግን በሁለቱ ቅዱሳን መጻሕፍት ለማርያም ጥያቄ የሰጡት መልስ በጣም የሰፋ ልዩነት አላቸው፣ እንዴት ቢባል በመጽሐፍ ቅዱስ "መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፣ መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑል ኃይልም ይፀልልሻል" ይላል።

እናንተ ክርስቲያኖች በኢአግንያን (አቴይስትስ) እና በተጠራጣሪዎች (ስኬፕቲክስ) ዘንድ ሊያሳጣችሁ የሚችል ክፍተት መፍጠራችሁ አልታያችሁምን? "እንዴት መንፈስ ቅዱስ በማርያም ላይ ሊመጣባት ይችላል? እንዴትስ የልዑሉ ኃይል ይፀልላታል?" ብለው ቢጠይቁስ? አገላለጡ በጥሬ ትርጓሜው (ሊትራሊ) ንጹሕ እርግዝናን (ኢማኩሌት ኮንሴፕሽን) የማይጠቁም ቢሆንም መንፈሱ ግን ወደዚያው የሚያመራ መሆኑን እኛ ሙስሊሞች እንረዳለን፣ ነገር ግን በዚህ አንቀጽ ሉቃ. 1 ቁ. 35 የሚገኙት ሐረጎች ጣዕመ ቢስ እንደሆኑ ይሰማናል፣ ይስማማሉ?

ዝነኛው አሜሪካዊ ሰባኪ ቢሊ ግራሃም ደርባን በሚገኘው "ኪንግ ፖርክ" ውስጥ በ4000 ሕዝብ ፊት ከላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ (ማቴ. 1 ቁ. 18) ድራማዊ በሆነ መልኩ ለማሳየት ሞክሯል፣ ጠቃሚ ጣቱን በማውጣትና የተዘረጋ ክንዱን ከቀኝ ወደ ግራ በማወናጨፍ "መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ማርያምን አስረገዛት" አለ፣ በሌላ በኩል ቅዱስ ሉቃስ ይህንን

www.ethiopianorthodox.org

ከማይታመንበት ቁርዓን ፍጹም እውነተኛና ትክክለኛ ነው ተብሎ ከሚታመንበት መጽሐፍ ቅዱስ የተሻለ ሊሆን ይችላል? የፈጣሪ ቃል ባይሆን ኖሮ የቄሱ ምርጫ ባልሆነ ነበር" ተብሏል።

የጆሐንስበርጉ ቄስ ደራሲው በአምሳሉ የፈጠረው የራሱ ደራሳ (ተማሪ) ሊሆን ይችላል፣ አንድ ቀን እንኳን ለክርስትና እምነቱ ሲያንገራግር ተሰምቶ አያውቅም፣ ሁል ጊዜ እጅን እንደሰጠ ነው፤ ደራሲው የፈጠረው ደቀ መዝሙር መሆኑን ገሐድ ያወጣው ቄሱ ከቁርዓንና ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ለሴት ልጅዎ የትኛውን ይመርጣሉ ተብሎ ቢጠየቅ የቁርዓኑን ታሪክ መረጠ ሲባል ነው፣ ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ ሆኖ ነው እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ የቁርዓን ታሪክ በየትኛው ቁምነገሩ ነው የሚሻለው?

ቅዱስ ቁርዓን የተጭበረበረና የተኮረጀ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን እውነተኛና ትክክለኛ ነው ሲሉ የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡት ወገኖች ሁለቱንም መጻሕፍት መርምረውና አመዛዝነው የተረዱ መሆን አለባቸው፣ ያለምክንያት "ተጭበርብሯል ተኮርጇል" የሚል ትችት አይሰነዝርበትም፣ "ካየያዝ ይቀደዳል፣ ካነጋገር ይፈረዳል"፣ "ከንግግርህ የተነሳ ትጸድቃለህ፣ ከንግግርህም የተነሳ ይፈረድብሃል" ይላል፤ ማቴ. 12 ቁ. 37።

እንደ ጆሐንስበርጉ ቄስ በችሎታቸው የማይተማመኑ ወይም ራሳቸውን ለጥቅም የሸጡ አንዳንድ ደካሞች በጓዘ ቀላልነቱ መርጠው ተከትለውት ይሆናል፣ "ከእኔ ጋር ያልሆነ ባለጋራዬ ነው፣ ከእኔ ጋርም አንድነት የሌለው ይበተናል" ማቴ. 12 ቁ. 30።



# የአዳም ቢጤና የጳውሎስ ፈጠራ

"የኢየሱስ ተአምራዊ አወላለድ "አምላክ" ወይም "የአምላክ ልጅ" ያደርገዋልን? የቁርዓን መልስ ፍጹም አሉታዊ ነው፣ አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ እንደ አዳም ቢጤ ነው፣ ከአፈር ፈጠረው፣ ከዚያም ለርሱ (ሰው) ሁን አለው፣ ሆነም፣ ቁርዓን 3 ቁ. 59፣

ባለፉት አንቀጾች ኢየሱስ እንደአንድ ነቢይ (መላክተኛ) የያዘው ክብርና ታላቅ ቦታ ከተገለጠልን በኋላ በአምላክነት ወይም የአምላክ ልጅነት ወይም ከሰው ልጅ በላይ ማንኛውንም ደረጃ መስጠትን በጥብቅ ሲቃወም እናነባለን፣ ኢየሱስ ያለሰብአዊ አባት መወለዱ እንደ መከላከያ ከቀረበ አዳምም ያለ አባት መገኘታቸው መታወስ አለበት፣ እንዲያውም አዳም ያለ እናትም ነው የተወለዱት፣ ሥጋችንን በተመለከተ የሁላችንም ቢሆን ያው ትቢያ አፈር መሆኑ ግልጥ ነው፣ በአላህ ፊት ኢየሱስ እንደ አዳም ሁሉ አፈር ወይም ሰብአዊ ነው፣ የኢየሱስ ታላቅነት የሚመነጨው (ሁን) የሚለው መለኮታዊ ትእዛዝ ነው፣ ምክንያቱም ከዚህ በኋላ ነበር ከአፈር የላቀ መንፈሳዊ መሪና አስተማሪ የሆነው፣

(አ. የሱፍ አሊ የቁርዓን ማብራሪያ በ3 ቁ. 59 ላይ የተሰጠ ማስታወሻ ቁ. 398) ክርስቲያናዊው ሉጅክ ከተባዕት (ወንድ) ወላጅ ውጭ መወለድ ከአምላክ እኩል የሚያደርግ ነው የሚል ከሆነ ለዚህ ታላቅ ክብር አዳም የበለጠ መብት አላቸው እንላለን፣ ግን አንድም ክርስቲያን ይህን አይቀበልም፣ ስለዚህ ሙስሊሞች የክርስቲያኖችን አግባብ ያልሆነ አስተሳሰብ ውድቅ እንዲያደርጉ ታዘዋል፣ በተጨማሪም ክርስቲያኖች አዳም ከጭቃ (የተፈጠረ) ሲሆን ኢየሱስ ግን በንጹሕ ፀዓዳ ሁኔታ በማርያም ማሕፀን ውስጥ መፀነሱን በመጥቀስ ፀጉር ስንጠቃ ከጀመሩ በራሳቸው ስንካላ መመዘኛዎች እንኳ ከኢየሱስ የላቀ ሰው እንዳለ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሶ እንደሚገኝ ልናስታውሳችሁ እንወዳለን፣ ይህ ታላቅና ልዩ ሰው ማነው?" በማለት ይጠይቅና መልከጼዴቅን ይጠቅሳል፣

www.ethiopianorthodox.org

ስሙንም ኢየሱስ ብለሽ ትጠሪዋለሽ፣ እርሱም ታላቅ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል፣ የዳዊት ያባቱን ዙፋን ይሰጠዋል፣ በያዕቆብ ወገን ለዘላለም ይነግሳል፣ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም" ሉቃ. 1 ቁ. 30።

እንግዲህ ከዚህ በላይ የተገለጠው ትንቢት የተቆጠረው ሱባኤ ጊዜው ሲደርስ (ሲፈፀም) መሢሕ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወረደ፣ ከድንግል ማርያም ተወለደ፣ ተወልዶም አዳነን፣ ሉቃ. 2 ቁ. 7።

"ክርስቲያኖች አዳም የተፈጠረ ከጭቃ ነው፣ ክርስቶስ ግን የተወለደው በንጹሕ ማሕፀን ተፀንሶ ነው በማለት በራሳቸው ሰንካላ መመዘኛዎች ፀጉር ስንጠቃ ከጀመሩ ከኢየሱስ የላቀ ሰው እንዳለ ከመጽሐፍ ቅዱስ ልንጠቅስላቸው እንወዳለን" በማለት የጽሑፉ አቅራቢ መልከጼዴቅን ጠቅሷል፣ ጥቅሱ "የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነ ይህ መልከጼዴቅ እናት አባት የለውም፣ ትውልዱም አይቆጠርም ለዘመኑ ጥንት ለሕይወቱ ፍጻሜ የለውም" .... ይልና "ይኸውላችሁ እንግዲህ ለመለኮታዊነት ሊቀርብ የሚችል እጩ የነኚህ ባሕርያት ባለቤት አላህ ብቻ ነውና" ይላል፣ ለመለኮታዊ ሥልጣን በእጩነት ሊቀርብ የሚገባው እነኚህ ባሕርያት ያሉት መልከጼዴቅ ነበር ለማለት ሞክሮ እንደገና የነኚህ ባሕርያት ባለቤት አላህ ብቻ ነው በማለት ሸውዷል።

እናንተ የሙስሊሙ አፈቀላጤዎች የዋሆች ወይም የአዋቂ አጥፊዎች ናችሁ፣ የመንግሥተ ሰማያትን በር ለመዝጋት የማትሮጡበት ሜዳ የማትገቡበት ቀዳዳ የለም፣ ግን ሜዳው ገደል ቀዳዳው አጣብቂኝ እየሆነ ከአሰባችሁበት ሳትደርሱ ወደ ኋላ ትመለሳላችሁ፣ የምትታገሉት ከእኛ ከክርስቲያኖች ጋር ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ነው፣ እግዚአብሔርም ራሳችሁ ከመጽሐፍ ቅዱስ በጠቀሳችሁት ኃይለ ቃል ግንባራችሁን እየፈቃ አሳፍሮ መልሷችኋል።

የጽሑፉ አዘጋጅ ይጠቅመኛል ብሎ ጠቅሶት ነገር ግን የሚያስረታው ስለሆነ ቆርጦ ያስቀረው ሙሉ ኃይለ ቃል



እንደሚከተለው ነው፣ ዕብራውያን 7 ቁ. 1-3 "ይህም መልከጼዴቅ የሳሌም ንጉሥ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነው፣ አብርሃምን የተገናኘው እርሱ ነገሥታትን ወግቶ በተመለሰ ጊዜ ባረከውም፣ አብርሃምም ከያዘው ሁሉ ካስር አንድ ሰጠው፣ የፊተኛውም የስሙ ትርጓሜ የጽድቅ ንጉሥ ነው፣ ከዚህም በኋላ የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ነው፣ አባት እናት የሉትም፣ ትውልዱም አይቆጠርም፣ ለዘመኑ መጀመሪያ ለሕይወቱ ፍጻሜ የለውም፣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ልጅ ምሳሌ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል" ይላል።

ጸሐፊው ይህን አንቀጽ የጳውሎስ ፈጠራ ብሎታል፣ ዶሮ የሌለው ፍየል ይንቃል፣ ጠብታ ያህል ጣዕመ ጸጋ ያልቀመሰ መናፍቅ የጳውሎስን መልዕክት ፈጠራ ነው ማለቱ ያስቃል፣ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጦለት ካህኑ መልከጼዴቅ ለእግዚአብሔር ልጅ ለክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ በብሉይ ኪዳን ቀደም ሲል የተጻፈውን ጥቢ አድርጎ አስተማረ እንጅ ፈጠራ አልነበረም፣ አብርሃም የአካባቢውን ነገሥታት ድል አድርጎ ሲመለስ መልከጼዴቅ ኅብስተ አኰቴት ጽዋዓ በረከት ይዞ ተቀብሎታል፣ አብርሃምም ከገንዘቡ ሁሉ ካስር አንድ አስራት በኩራት ቀዳማያት ሰጥቶታል።

ከላይ እንደተጠቀሰው መልከጼዴቅ ለእግዚአብሔር ልጅ ምሳሌ መሆኑን የሚያስረዳው "ለዘመኑ ጥንት ለሕይወቱ ፍጻሜ የለውም" የሚለው ኃይለ ቃል ነው፣ መልከጼዴቅ አይሞትም ለዘላለም ይኖራል ማለት ነው? አይደለም፣ መልከጼዴቅ ሰው እንደመሆኑ መጠን ሞቷል ተቀብሯል፤ ትውልዱና ነገዱ አይታወቅም ማለቱ እስራኤላዊ ስላልነበረ ነው፣ መልከጼዴቅ ትውልዱ ኢትዮጵያዊ ነው፣ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ለማረጋገጥ ቃሉ እንደሚያመለክተው ከመልከጼዴቅ (መልአከ ጽድቅ) ጀምሮ የኢትዮጵያ ነገሥታት የሰላም ንጉሥ ሥዩመ እግዚአብሔር እየተባሉ ሲገዙ ኖረዋል፣ መልከጼዴቅን የሰላም ንጉሥ የሥልጣነ ክህነት ጀማሪ ካህን አድርጎ የሾመው እግዚአብሔር ነው" ዘፍ 14 ቁ 18።



www.ethiopianorthodox.org

አዳም መጀመሪያ አለው (ጀነት) ኢየሱስም መጀመሪያ አለው (በረት)፣ አዳም መጨረሻ አለው፣ ኢየሱስም እንደዚሁ፣ ዳሩ ግን መልከጼዴቅ የት እንዳለ አይታወቅም ተብሏል፣ አዳም መጀመሪያና መጨረሻ ቢኖረውም ገነት አይደለም፣ መጀመሪያው መሬት መጨረሻው ሞት ነው፣ የመልከጼዴቅም ፍጻሜ ሞት ነው፣ ክርስቶስ ግን መጀመሪያና መጨረሻ የለውም፣ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት የነበረ ያለ ወደፊትም የሚኖር ለዘመኑ ጥንት ለሕይወቱ ፍጻሜ የሌለው የባሕርይ አምላክ ነው፤ ራዕ. 1 ቁ. 8።

ክርስቶስ ከአፈር አልተፈጠረም፣ ልብ-ወለድ ነው፤ ሌላው ቀርቶ ቁርዓን እንኳ ከአፈር ተፈጠረ አላለም፣ አላህ ሁን ብሎት ከማርያም ተወለደ ይላል፤ ቁርዓን 3 ቁ. 45፤ በሞተ ጊዜም እንደሰው አፈር ትቢያ ሆኖ አልቀረም፣ በተቀበረ በሦስተኛው ቀን በተላቅ ኃይል ተነስቶ ወደሰማይ ዓርጓል፣ በአባቱ ቀኝ በጌትነት ክብሩ ተቀምጧል፤ ማር. 16 ቁ. 4-6።

ዕብራውያን ማለት እስራኤላውያን ማለት ነው፣ ኤቦር የሚባል አባት ነበራቸው፣ በኤቦር ዕብራውያን ተብለዋል፣ የጳውሎስ የመልዕክቱ ስም በዕብራውያን (እስራኤላውያን) ስም ተሰይሟል ማለት ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ራሱን አስራ ሦስተኛ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር አድርጎ ሾሟል ተብሏል፣ ውሸት ነው፣ በመሠረቱ ሐዋርያት 12 ናቸው፣ ከ12 አንዱ ይሁዳ በፍቅረ ንዋይ ተታልሎ መምህሩን ክርስቶስን (በሠላሳ ብር) በመሸጡ ከቁጥር ወጣ፣ ክርስቶስ ከሞተ በኋላ ሐዋርያት ተሰብስበው በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት በጸሎት ማትያስ የተባለውን ደቀ መዝሙር መርጠው የይሁዳን ቦታ እንዲተካ አድርገዋል።

"ቅዱስ ጳውሎስ በኢየሱስ ትምህርቶች ላይ ትልቅ ዝብርቅርቅ በማምጣቱ የሁለተኛ ደረጃ ሊያገኝ ችሏል" ተብሏል፣ መቸም እናንተ የሙስሊሙ አፈቀላጤዎች የክርስቶስን ክብር ያሳነስን እየመሰላችሁ የማትሸርቡት ገመድ የማትቆፍሩት ጉድጓድ የለም፣ ስለ ክርስቶስ



አዳኝነት አስፋፍቶ የመሰከረና ያስተማረ ሁሉ በእናንተ ዘንድ ጥፋተኛ ነው፣ ቅዱስ ጳውሎስ ከሌሎቹ ባልንጀሮቹ ይልቅ አብዝቶ 14 መልዕክት የጻፈ ስለክርስቶስ አምላክነትና አዳኝነት በሰፊው ያስተማረ መናፍቃንን ያሳፈረ፣ ለስብከተ ወንጌል ቀልጣፋ፣ ከታናሽ እስያ አምልኮ ባዕድን ያጠፋ፣ የሃይማኖት መዶሻ፣ የአሮጌው ሥርዓት ማፍረሻ ታማኝና ምርጥ የክርስቶስ ወታደር መሆኑን በተግባር ያስመሰከረ መንፈሳዊ አርበኛ ነው።

እውነቱን ለመናገር ከተፈለገ ዝብርቅርቅ ትምህርት የምታስተምሩ እናንተው አፈቀላጤዎች ናችሁ፣ ለቆማችሁለት ዓላማና ለዚህ ጉንጭ አልፋው ክርክራችሁ መፋለሚያ ልታደርጉት ፈልጋችሁ መነሻና መድረሻውን መውጫና መግቢያውን የማታውቁትን መጽሐፍ ቅዱስ እንደፈለጋችሁ እየጠቀሳችሁ የላዩን ወደታች የታቹን ወደላይ በማድረግ የምታዘበራርቁት እናንተው አፈቀላጤዎች ናችሁ እንጂ ቅዱስ ጳውሎስ ዝብርቅርቅ ትምህርት አላስተማረም፣ ትምህርቱ ዝብርቅርቅ ለመሆኑ የተጠቀሰ ማስረጃ የለም፣ ባጭር ታጥቆ መናፍቃንን የተዋጋ የሐሰተኞችን አንደበት የዘጋ ከሐዋርያት መካከል የላቀ ምርጥ ጀግና ቅዱስ ጳውሎስ ነው።

ወደፍጻሜ ዘመኑ አካባቢ "መልካሙን ገድል ተጋደልሁ፣ ሩጫዬንም ጨረስሁ፣ ሃይማኖቴንም ጠበቅሁ፣ እንግዲህ እግዚአብሔር የሚሠጠኝ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፣ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክበኛል፣ ለእኔ ብቻ አይደለም፣ መገለጡን ለሚወድ ሁሉ እንጂ" ሲል ከሚታዩና ከማይታዩ የክርስትና ጠላቶች ጋር ያደረገውን መንፈሳዊ ተጋድሎና በኋላ ጊዜ የሚያገኘውን ሰማያዊ ክብር በራሱ አንደበት በኩራት ተናግሮታል፣ 2 ጢሞ. 4 ቁ. 7።

ጳውሎስ አያሌ መልዕክቶችን በመጻፍ አሸናፊ ሆኗል፣ ኢየሱስ ግን አንድም ቃል አልጻፈም፤ ጳውሎስ መልዕክቶቹን ለመጻፍ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አላስፈለገውም" ተብሏል፤ አፈቀላጤዎች አልተረዳችሁትም እንጂ ክርስቶስ ብዕር ቀርጦ ቀለም በጥብጦ የክርስትናን ትምህርት ወንጌልን በደሙ ጽፎ በሐዋርያት አጥንት



www.ethiopianorthodox.org

በክርስቶስ ስም በመስጊድ ውስጥ አስተማረ፣ እርሱ (ክርስቶስ) የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ" የሐዋ. ሥራ 9 ቁ. 1-20።

እንግዲህ ክርስቶስ ቅዱስ ጳውሎስን ከላይ እንደተገለጠው በመብረቅ ኃይል አስገድዶና አስጨንቆ ከአሪት ሥርዓት ወደ ወንጌል ትምህርት ከጠራው በኋላ "ምርጥ ዕቃ" የሚል ስያሜ ሰጥቶታል፣ እንደ ጳውሎስ ያሉትን ምርጥ የክርስቶስ ወታደሮች ያለስማቸው ስም ያለሥራቸው ሥራ እየሰጡ ማጥላላት ትርፉ ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ነው፣ ክርስቶስ ሳውልን በጠራው ጊዜ "በተሳለ ሰለት ላይ ብትቆም አንተን ይጎዳሃል እንጂ ሰለቱ አይጎዳም" ብሎ እንደተናገረው የሙስሊሙ አፈቀላጤዎችም ክርስትናን ያዳከምን እየመሰላቸው የሚፈጽሙት ድርጊት ራሳቸውን ይጎዳል እንጂ የወንጌልን ሐዋርያዊ ጉዞ ሊያሰናክል አይችልም፣ "ስለስሜ በሁሉም ዘንድ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፣ እስከፍጻሜ የሚታገስ ግን እርሱ ይድናል" ማቴ. 10 ቁ. 22።

ጸሐፊው "ከዚህ ላይ ኢየሱስ የተናገራቸውን ቃላት መጥቀሱ ተገቢ ነው" ካለ በኋላ ማቴ. 13 ቁ. 13 ላይ "እያዩ ስለማያዩ እየሰሙ ስለማይሰሙ ስለማያስተውሉም በምሳሌ እነግራቸዋለሁ" የሚለውን ጠቅሶ ቁርዓንም 2 ቁ. 12 "እነሱ ደንቆሮዎች ዲዳዎችና ዕውሮች ናቸው፣ ስለዚህ እነሱ አይመለሱም" የሚለውን ተመሳሳይ አንቅጽ አክሎ ክርስቲያኖች እስልምናን ባለመቀበላቸው ያወግዛል ይኮንናል፤ ክርስቶስ ይህን የኢሳይያስን ትንቢት ጠቅሶ ያስተላለፈው ተግሣፅ አምላክነቱን በሥራ እየገለጠ ቢያስተምራቸው ትምህርቱን አንቀበልም በማለት ዓይናቸውን ጨፍነው ጆሮአቸውን ደፍነው ያስቸገሩትን አይሁድ ሊገሥፅበት ነው፣ ዛሬም እናንተ የሙስሊሙ አፈቀላጤዎች አይሁድ በክርስቶስ አዳኝነት ላይ ከፍተውት የነበረውን የተቃውሞ ዘመቻ እየደገማችሁት ነው፣ ከዚህ የተነሳ ቁርዓንም ሆነ ወንጌል "እያዩ የማያዩ፣ እየሰሙ የማይሰሙ ዕውሮች ዲዳዎችና ደንቆሮዎች" አያሉ የሚነቅፉችሁና የሚዘልፏችሁ እናንተኑ ነው፣ ሐሜት ወደ መጣበት ይመለስ።



# የአምላክ ልጆች

"Jesus the only begotten son, begotten not made" የሚለው የክርስቲያኖች እምነት ከሙስሊሞች ምንጊዜም የሚያጋጥመው ጠንካራ ተቃውሞ ነው፣ ይህ እምነት ክርስቲያኖች ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በምሥጢረ ሥላሴ እንደዳዊት እንዲደግሙት የሚደረግ ነው፣ "BEGOTTEN NOT MADE" ሲሉ ምን ማለታቸው እንደሆነ የክርስቲያንን ምሁራን በተደጋጋሚ ጠይቄአለሁ፣ ከአምላክ በተሰጣቸው (?) የራሳቸው መጽሐፍ ውስጥ እንደተገለጠው አላህ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ልጆች እንዳሉት ሳይገነዘቡ አልቀሩም፤

"....የአዳም ልጅ፣ የእግዚአብሔር ልጅ" ሉቃስ 3 ቁ. 38፣

"የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደሆኑ አዩ"፣ ዘፍ. 6 ቁ. 2፣

"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ እስራኤል የበኩር ልጄ ነው" ዘፀ. 4 ቁ. 22፣

"እኔ ለእስራኤል አባት ነኝና፣ ኤፍሬምም በኩሬ ነውና" ኤርምያስ 31ቁ. 9፣

"ትእዛዙን እናገራለሁ፣ እግዚአብሔር አለኝ አንተ ልጄ ነህ፣ እኔም ዛሬ ወለድሁህ" መዝ. 2 ቁ. 7፣

"በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና" ሮሜ 8 ቁ. 14 በማለት ጸሐፊው "ለእግዚአብሔር ልጅ የለውም" ለሚለው እስላማዊ ፍልስፍና በማስረጃነት ይጠቅመኛል ብሎ ጠቃቅሶ አቅርቧል።

<u>መልስ፣</u> መቸም የክርስቶስ አምላክነትና የእግዚአብሔር ልጅነቱ እገሌ እገሌን ቢወልድ ተብሎ ዘር ቆጥሮ የሚደረስበት የዘር

www.ethiopianorthodox.org

ያመነች ብቸኛ የክርስትና ደሴት ናት፤ ዛሬም ያልተበረዘ ያልተከለሰ የሥነ መለኮት ትምህርት የሚሰጥባት የጠሩ ቀለም የሚገኝባት የዓለም ዓቀፉ ክርስትና የሃይማኖት መረጃ ናት፤

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀመዛሙርቱ በሞት ከመለየቱ በፊት የምነግራችሁ ብዙ አለኝ፤ ነገር ግን አሁን ትሸከሙት ዘንድ አትችሉም ሲል ለደቀመዛሙርቱ የመንፈስ ተሐድሶ እንደሚያስፈልጋቸው ነግሯቸዋል፤ እንደዚሁም የሙስሊሙ አፈቀላጤዎች በጥምቀት (በመንፈስ ቅዱስ) ሳትታደሱ መቀበሉ ይከብዳችኋል እንጂ በየገሩ ዞረን አጣነው ያላችሁትን የሥነ መለኮት ትምህርት ባጭሩ አቀርብላችኋለሁ፤ የሥነ መለኮት ትምህርት ማለት ምሥጢረ ሥላሴ ምሥጢረ ሥጋዌ ምሥጢረ ጥምቀትና ........ የመሳሰሉት ናቸው፤ ምሥጢር መባሉ በዓይን የማይታይ በእጅ የማይዳሰስ በምርምርና በጥናት የሚደረስበት ረቂቅ ፍልስፍና በመሆኑ ነው፤

## ምሥጢረ ሥላሴ

"begotten not made" በግዕዙ "ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ" "ኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጠረ ያይደለ ብቸኛ የእግዚአብሔር ልጅ ነው" ለሚለው የሥነ መለኮት ፍልስፍና ምርምርና ጥናት ወደ ምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት ይወስደናል፤

ሥላሴ በስም በአካል በግብር ሦስት ናቸው፤ ስማቸው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይባላል፤ የአብ አካል አለው፤ የወልድ አካል አለው፤ የመንፈስ ቅዱስ አካል አለው፤ ግብራቸውም አብ ወላዲ ወልድ ተወላዲ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ነው፤ የአብ ግብሩ መውለድ ማሥረፅ ነው፤ የወልድ ግብሩ መወለድ ነው፤ የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መሥረፅ ነው፤ ሥላሴ ሦስት ስም ሦስት አካል ሦስት ግብር ስላላቸው ሦስት አማልክት ማለት አይደለም፤ ሦስቱም በባሕርይ በሕልውና ይህን ዓለም በመፍጠርና በመግዛት አንድ ናቸው፤ አንዱ ካንዱ አይቀድምም፤ አንዱ ካንዱ አያንስም፤ ሥጋዊ አባት ከልጁ



እንደሚበልጥና እንደሚቀድም አብ ወልድን አይበልጠውም አይቀድመውም፤ ወልድም ካባቱ አያንስም፤ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ከወለድ ጋር እኩል ነው፤ ሥላሴ በፀሐይ ይመሰላሉ፤ ለፀሐይ ሦስት ግብር አለው፤ ብርሃኑ ሙቀቱና ክበቡ ነው፤ አብ በክበቡ ወልድ በብርሃኑ መንፈስ ቅዱስ በሙቀቱ ይመሰላሉ፤ ፀሐይ ሦስት ግብር አለው ስለተባለ ሦስት ፀሐይ አይባልም፤ አንድ ፀሐይ ይባላል እንጂ፤ ሥላሴም ሦስት ስም ሦስት አካል ስላላቸው ሦስት እግዚአብሔር ማለት አይደለም፤ አንድ እግዚአብሔር ይባላሉ እንጂ፤

ሥላሴ አንድም ሦስትም በመሆናቸው ከብሉይ ኪዳንና ከሐዲስ ኪዳን ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፤ ከብሉይ ኪዳን "እግዚአብሔርም አለ፤ በመልካችን እንደምሳሌያችን ሰውን እንፍጠር" ብሏል፤ "እግዚአብሔር አለ" ሲል ያንድ ሰው ድምፅ ነው፤ "በመልካችን እንደምሳሌያችን ሰውን እንፍጠር" ሲል ደግሞ የብዙ ሰዎች ድምፅ ነው።

"እግዚአብሔር አምላክም አለ፤ እነሆ! አዳም ከእኛ እንዳንዱ ሆነ፤ መልካሙንና ክፉውን የሚያውቅ" ብሏል፤ "ከእኛ እንዳንዱ" ሲል እግዚአብሔር ካንድ በላይ መሆኑን ያስረዳል።

"ኑ እንውረድ ቋንቋቸውንም እንለያይባቸው፤ አንዱ የሌላውን ቋንቋ እንዳይሰማ አለ እግዚአብሔር" "ኑ እንውረድ እንለያይባቸው" ሲል የብዙ ሰዎች ድምፅ ነው፤"አለ" ሲል ያንድ ሰው ድምፅ ነው፤ ከነዚህ የተሻለ ግልጥ ማስረጃ አለ፤ ይኸውም "አብርሃም በመምሬ ዓፀድ ተቀምጦ ሳለ አሻግሮ ሲመለከት እነሆ ሦስት ሰዎች ወደርሱ ሲመጡ አየ፤ ከድንኳኑ ደጅ ሊቀበላቸው ሮጠ፤ ወደምድርም ሰገደ፤ አቤቱ! በፊትህስ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ እለምንሃለሁ፤ ባሪያህን አትለፈኝ ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁና እግራችሁን ታጠቡ፤ ከዚች ዛፍ በታች እረፉ፤ ቁራሽ እንጀራ ይምጣላችሁና ልባችሁን ደግፉ፤ ከዚያ በኋላ ትሄዳላችሁ፤ ..... አላቸው" ይላል፤ "ሦስት ሰዎች" ሥላሴ ናቸው፤ "አትለፈኝ" ሲል አንድነታቸውን ያስረዳል፤ ይህ ከብሉይ ኪዳን የተገኘ



www.ethiopianorthodox.org

ግልጥ ማስረጃ ነው፤ ዘፍ 1 ቁ. 16፤ 11 ቁ. 1-7፤ 18 ቁ. 1-5 ተመልከት።

ከሐዲስ ኪዳን ደግሞ "ክርስቶስ ሲጠመቅ አብ በደመና ሆኖ የምወደው ልጄ ይህ ነው ደስታዬን የምገልጥበት በማለት ሲመሰክር፣ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥበት በግልጥ ታይቷል፤ በመጨረሻ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ ሥልጣን ሰጥቶ ሲያሰናብታቸው "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፤ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው፤ በዚህም ያዘዝኋችሁን ሁሉ አስተምሯቸው፤ እኔም እነሆ በዘመኑ ሁሉ እስከ ዓለም ፍጻሜ ከናንተ ጋራ ነኝ" ብሏቸዋል፤ እስከዚህ ምሥጢረ ሥላሴ ነው፤ ማቴ. 3 ቁ. 13-17፤ 28 ቁ. 19።

## ምሥጢረ ሥጋዌ

ከሥነ መለኮት ሊቃውንት አንዱና አንጋፋው ወንጌላዊው ዮሐንስ ስለምሥጢረ ሥጋዌ የጻፈው መሠረተ ትምህርት እንደሚከተለው ነው፤

"አስቀድሞ ቃል ነበረ" ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ እግዚአብሔርም ቃል ነበረ፤ ይህ አስቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፤ ሁሉም በርሱ ሆነ፤ ያለርሱ ምንም የሆነ (የተፈጠረ) ነገር የለም፤ ሕይወት በርሱ ነበረች፤ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች ካለ በኋላ ዝቅ ብሎ ".... ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በእኛም አደረ፤ ክብሩንም አየን፤ ለአባቱ አንድ ልጅ እንደመሆኑ ፀጋና እውነትም የመላበት" ይላል፤ ዮሐ. 1 ቁ. 1-14።

ይህ ከዚህ በላይ የተነገረው ኃይለ ቃል ለሥነ መለኮት ፍልስፍና የማዕዘን ራስ ነው፤ ወንጌላዊው እንደተናገረው ከዓለም በፊት የነበረ ቃል ሥጋ ሆነ፤ በእኛም አደረ ማለት ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ተወለደ፤ ያ ቃል ሥጋ ከመልበሱ (ከድንግል ማርያም ከመወለዱ) በፊት ያለእናት ካባት ብቻ ተወልዷል፤ እንግዲህ ይህ ነው ለሙስሊሞቹ የማይቆረጠም የድንጋይ ቆሎ የማይዋጥ የብረት እሎሎ ሆኖ የሚያውካቸው፤ "እግዚአብሔር እንዴት ልጅ ይወልዳል? እንዴትስ ልጅ አለው ይባላል? በማለት አጥብቀው ይቃወማሉ፤ ነገር ግን ሙስሊሞች ያልደረሱበትና ሊረዱት የሚገባቸው ምርምር አለ፤ ኢየሱስ ከድንግል ማርያም በድንግልና መወለዱን አምነው ይቀበላሉ፤ እንግዲያውስ እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል፤ ስለዚህ ሴትስ ያለአባት እንዴት ልጅ ልትወልድ ትችላለች? ይህስ አይገርምም? አያስደንቅም? ታዲያ ሴትን ያለአባት ልጅ እንድትወልድ ያደረገ እግዚአብሔር ከባሕርዩ ልጅ ማስገኘት እንዴት ይሳነዋል? ሌላም እግዚአብሔር የሠራው እኛ ግን ባለማስተዋል በተለምዶ ሳናውቀው ሳናደንቀው የሚኖር አንድ አምላካዊ ክንውን አለ፤ ይኸውም እግዚአብሔር ይህን ዓለም "እምኀበ አልቦ ኀበ ቦ" (ካለመኖር ወደ መኖር) አምጥቶ መፍጠሩ ዕፁብ ድንቅ የሚባል አይደለምን? እንግዲህ እነዚህ ሁለት ዓበይት ክንውኖች ማለት ሴት ያለአባት ልጅ እንድትወልድ ማድረግና ይህን ግዙፍ ዓለም ማለት (ምድርን ከነልብሱ ሰማይን ከነግሱ) ማስገኘት የቻለ እግዚአብሔር ከባሕርዩ ልጅ ማስገኘት እንዴት ይሳነዋል? አይሳነውም፤ ስለዚህ ይህ ከድንግል ማርያም ያለአባት መወለዱ (ድኅራዊ ልደቱ) ቀድመ ዓለም ያለእናት ካባት ብቻ መወለዱን (ቀዳማዊ ልደቱን) ሊያረጋግጥልን ይችላል ማለት ነው፤

ስለ ቀዳማዊ ልደቱ (ካባት ብቻ ስለመወለዱ) ብሉይ ኪዳን የሰጠው ማረጋገጫ አለ፤ "ማናቸውም ነገር ሳይፈጠር እኔ ነበርሁ፤ ከጥንት ጀምሮ ለዘላለም ተሾምሁ፤ ወንዞች ተራሮችና ኮረብቶች ሳይመሠረቱ ተወለድሁ" "እግዚአብሔር ልጄ ነህ አለኝ፤ እኔም ዛሬ ወለድሁህ" ይላል፤ ምሳ. 8 ቁ. 22-25፤ መዝ. 2 ቁ. 7፤

የአብ አባትነትና የወልድ ልጅነት በዚህ ጊዜ በዚህ ስፍራ ተጀመረ ብለን ጊዜና ቦታ ለይተን ወስነን መናገር አንችልም፤ ምክንያቱም ይህን አምላካዊ ጥበብ የሰው ልጅ አእምሮ መርምሮ ሊደርስበት ስለማይችል ነው፤ አብ ልጁን "ውረድ ተወለድ ሙት



www.ethiopianorthodox.org

ደጉን ለይታችሁ ታውቃላችሁ (እንደርሱ አምላክ ትሆናላችሁ) አሁን ማድረግ ያለብሽ የዚችን እንጨት ፍሬ በጥሰሽ አዘጋጅተሽ አዳም ሲመጣ ተመገቡት፣ ስተመገቡትም ሁለታችሁ እኩል ተመገቡት፣ ለባልሽ በቀኝ እጅሽ ስታጎርሽው በግራ እጅሽ ደግሞ አንች ጉረሽ አላት፣ ሔዋንም በፊቷ ተንገርግጋ ከመታስጎመገፖት ዕፀ በለስ ፍሬ በፍጥነት በጠሰችና ካዘጋጀች በኃላ አዳም ከዋለበት ሲመጣ ቀደም ሲል ከሳጥናኤል በተሰጣት መመሪያ መሠረት ባንድ እጇ ለአዳም ስታጎርሰው በሌላው እጇ ደግሞ ለራሷ ጎረሰች፣ በዚህ ጊዜ ዓይናቸው ተከፈተ፣ ራቁታቸውን መሆናቸውን አወቁ፣ መተፋፈር መጣ፣ ሁለቱም ደንግጠው ሐፈረታቸውን በቅጠል ሸፈኑ፣ ዘፍ 3 ቁ. 1-7።

"እግዚአብሔር አምላክም አለ፣ እነሆ አዳም ከእኛ እንዳንዱ ሆነ፣ መልካሙንና ክፉውን የሚያውቅ፣ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ ከሕይወት ዛፍም ወስዶ እንዳይበላ፣ ለዘላለም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፣ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ከዔደን ገነት አወጣው፣ የተፈጠረባትን ምድር ያርስ ዘንድ" ዘፍ. 3 ቁ. 22-23፣

አዳም ከእግዚአብሔር ጋር ተጣላ፣ ከገነት ወጣ፣ ክብሩን አጣ፣ ከዚህ የተነሳ ምርር ብሎ አለቀሰ፣ እግዚአብሔርም ልቅሶውን ሰምቶ አዘነለት፣ "በአምስት ቀን ተኩል መጥቼ አድንሃለሁ" ሲል ቃል ኪዳን ገባለት፣ አዳም አምስት ቀን ጠብቆ በስድስተኛው ቀን አጋማሽ ላይ እግዚአብሔር የሚመጣበትን ሰዓት ሲጠባበቅ እግዚአብሔር እንደገና ተገልጦ አምስት ቀን ተኩል ማለት አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ማለት ነው፣ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በመስቀል ላይ ተሰቅዬ ሥጋዬን ቆርሼ ደሜን አፍስሼ አድንሃለሁ ሲል የማዳን ተስፋውን አብስሮታል፤ "ነገር ግን ይህ ነገር ከናንተ አይሰወር፣ ወዳጆቸ ሆይ! አንድ ቀን በእግዚአብሔር ዘንድ 1000 ዘመን ነው፣ 1000 ዘመንም አንድ ቀን ነው፣ የእግዚአብሔር ተስፋ አይዘገይም፣ ሰዎች ይዘገያል እንደሚመስላቸው" 2ጴጥ. 3 ቁ. 8፣ መዝ. 90 ቁ. 4።



www.ethiopianorthodox.org

አዳምና ሔዋን ከገነት ከወጡ በኋላ ከነልጅ ልጆቻቸው የበደሉትም ያልበደሉትም በጠላታቸው በሳጥናኤል ቁጥጥር ሥር ሆነው ያችን የመዳን ቀን በተስፋ ሲጠባበቁ ኖሩ፣ "ነገር ግን ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ያሉትን ሞት ሠለጠነባቸው፣ በበደሉትም ባልበደሉትም ላይ፣ ሁሉ በአዳም ምሳሌ በኃጢአት ተፈጥሯልና፣ አዳምም ይመጣ ዘንድ ላለው (ለክርስቶስ) ምሳሌ ነውና" ሮሜ 5 ቁ. 14፣ 1 ቆሮ. 15 ቁ. 21-22።

እግዚአብሔር ለአዳም በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈፀም አንዲት ደቂቃ አላሳለፈም ከሥላሴ አንዱ ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወረደ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ (ተዋሕዶ) በቤተልሔም ተወለደ፣ እንደሕፃናት ቀስ በቀስ አደገ፣ በ30 ዘመኑ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ፣ እህል ውሀ ሳይቀምስ 40 ቀንና 40 ሌሊት ጾመ፣ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ወንጌልን አስተምሮ በመጨረሻ በዕለተ ዓርብ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ በሞቱ ሞትን ደምስሶ አዳምን ከነልጅ ልጆቹ ከሳጥናኤል አገዛዝ (ከሲኦል) ነፃ አወጣው፣ በጠላቱ ተንኮል ያጣውን ገነት የተነጠቀውን ልጅነት መለሰለት፣ የሐዋ. 2 ቁ. 31፣ 1 ቆሮ. 15 ቁ. 54-57።

እንግዲህ አዳምና ሔዋን የተሰጣቸውን ትእዛዝ ባለማክበራቸው ከፈጣሪያቸው መጣላታቸውን ከገነት መውጣታቸውን ሙስሊሞችም ታውቃላችሁ፣ ታዲያ አዳምና ሔዋን ከፈጣሪያቸው እንደተጣሉ ከገነት እንደወጡ ቀርተዋል? ወይስ ታርቀዋል? ከታረቁስ እንዴት? በምን ሊታረቁ ቻሉ? ለዚህ ጥያቄ ከሙስሊሙ ምሁራን አጥጋቢ መልስ እናገኛለን ብለን ተስፋ አናደርግም፣ ስለዚህ ከፍ ብሎ በተሰጠው ትምህርታዊ ማብራሪያ ተስማምተን በእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ ደም እንታረቅ እላችኋለሁ።

ኢየሱስ የፈጣሪ ብቸኛ ልጅ ነው (**The only begotten son of God**) የሚለውን ክርስቲያናዊ ፍልስፍና ለማስረዳት ምሥጢረ ሥላሴን ምሥጢረ ሥጋዌንና በኋላም ከሥላሴ አንዱ ወልድ ሰው

የሆነበትን ምክንያት ተንትኖ ማስርዳት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከኔ ጋር በትዕግስት አብራችሁ ብዙ እንደተጓዛችሁና ጠቃሚ ትምህርት እንደቀሰማችሁ ተስፋ በማድረግ አሁን ወደ ጸሐፊው ዝግጅት እመልሳችኋለሁ።



## ስድስተኛ ምዕራፍ

## “ምላሽ ለሕዝበ ክርስቲያን ውዥምብር”

“ክርስቶስ በኢስላም” የሚለው ርዕስ የክርስቶስ ማንነት በቁርዓን በግልፅ ከመስፈሩ አንፃር “ክርስቶስ በቁርዓን” ቢባል የበለጠ ተስማሚ ነው፣ ቁርዓን በክርስቶስ ዙሪያ ለሚሽከረከሩት ጥቄዎች ትክክለኛውን ምላሽ ሰጥቷል፣ አላህ (ሱ.ወ) በቁርዓን ኢየሱስን ከጠላቶቹ መሠረተ ቢስ ክስና ከየዋህ ተከታዮቹ ጣሪያ የነካ ውዳሴ ነፃ አድርጎታል፣ ጠላቶቹ (አይሁድ) ኢየሱስ መለኮታዊነትን በማወጅ አምላክን ተጋፍቷል እያሉ ሲወርፉት የርሱ ተከታዮች ነን ባዮች (ክርስቲያኖች) ደግሞ እርግጥ ነው ኢየሱስ መለኮታዊነትን አውጇል፣ ሆኖም እምላክ ነውና አምላክን አልተጋፋም ይላሉ፣ ቁርዓንስ ስለዚህ ጉዳይ ምን ይል ይሆን? ይህን የአይሁድና የክርስቲያኖች እሰጥ አገባ አስመልክቶ አላህ እንዲህ ይላል፣ “እናንት የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፣ በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገሩ፣ የመርየም ልጅ አልመሢሕ ኢሳ የአላህ መላክተኛ ወደመርየም የጣላት (የሁን) ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው፣ በአላህና በመላክተኞቹ እመኑ ....” በማለት እውነታውን ይፋ አድርጎታል ብሏል፣

<u>መልስ፣</u> በክርስቶስ ዙሪያ ተገቢ ያልሆኑ ጥያቄዎችን የመታሽከረክሩ እናንተው ሙስሊሞች ናችሁ፣ ቁርዓን በክርስቶስ ትምህርት ላይ አፍራሽ ተልዕኮ ያለው እውነትን በሐሰት እየለወጠ ውዥምብር የሚነዛ ለራሱ በራሱ የቆመ እንጂ ስለክርስቶስ ማንነት በማስረጃነት (በዋቢነት) መቅረብ የሚችል አይደለም፣ መሠረተ ቢስ ክስም የመሠረታችሁበት እናንተው የሙስሊሙ አፈቀላጤዎች ናችሁ፣ የክርስቶስን አዳኝነት በመቃወምና ባለመቀበል አንፃር በአይሁድና በእናንተ በሙስሊሞች መካከል ምን ልዩነት አለ? አይሁድ አምላክነቱን በሥራ እየገለጠ ማለት ድውይ እየፈወሰ ሙት እያስነሳ ዕውር እያበራና ሌላም ሥራ እየሠራ ቢያስተምራቸው



www.ethiopianorthodox.org

እንዲህ ሲሉ ወራሹ ይህ ነው፣ ኑ እንግደለውና ርስቱን እጅ እናድርግ፣ ያዙትም ከወይኑ ወደሚዳ አወጡና ገደሉት" ይላል፣ ማቴ. 21 ቁ. 23።

ይህ ግልጥ ምሳሌ ነው፣ ቀደም ሲል እነአብርሃም እነሙሴ መነሳታቸውን፣ በኋላም ነቢያት ደቂቀ ነቢያት ወደ እስራኤል መላካቸውን፣ እስራኤልም በየጊዜው የተነሱትን ነቢያት እየያዙ ማሰራታቸውንና መግደላቸውን በመጨረሻም እግዚአብሔር አንድ ልጁን ልኮ አምላክነቱን መድኃኒትነቱን ቢያስተምራቸው ጠልተው ተመቅኝተው ሰቅለው መግደላቸውን ያስረዳል።

ወንጌላዊው ዮሐንስ አካል ከሕልውና ተገልጦለት "ቃል ሥጋ ሆነ" በማለት የጻፈውን ለምሥጢረ ሥጋዌ መሠረት ለመናፍቃን ራስ ምታት የሆነውን ይህን ኃይለ ቃል የሙስሊሙ ኅብረተሰብ አፈቀላጤዎች "ትብትብ ነው" የጻፈውም ሌላ ሰው ነው ብለዋል፣ መቸም መናፍቃን ምላሽ የሚያሳጣ ኃይለ ቃል ሲገጥማቸው ጸሐፊውን ማጥላላት ያለሥራው ሥራ ያለስሙ ስም መስጠት ልማዳቸው ነው።

ቀደም ሲል ሐዋርያው ጳውሎስ መልከጼዴቅ የእግዚአብሔር ልጅ ምሳሌ ነው ብሎ ቢጽፍ የጳውሎስ ፈጠራ ነው ብሎት ነበር፣ አሁን ደግሞ ወንጌላዊው ዮሐንስ "ቃል ሥጋ ሆነ" ብሎ የጻፈውን ትብትብ ነው ብሎታል፣ ይሁን እንጂ ስለምሥጢረ ሥጋዌ ምንም ዓይነት ግንዛቤ የሌላቸው መናፍቃን ያሉትን ቢሉ ወሬ ቢቀጣጥሉ "የቃል ሥጋ ሆነ ምሥጢር" ሰው ሠራሽ ባለመሆኑ ፀሐፊውም ሆነ ኃይለ ቃሉ አይለወጥም፣ አይናወጥም።

"እግዚአብሔር አንድ ነው አይወርድም አይወልድም" ብሎ ማመን እጅግ በጣም ቀላል ፍልስፍና ሲሆን፣ "ሥላሴ አንድም ሦስትም ናቸው"፣ "አምላክ ወረደ ተወለደ" ብሎ ማመን ግን እጅግ በጣም ከባድ ፍልስፍና በመሆኑ ጥልቅ ምርምርና ጥናትን ስለሚጠይቅ የሙስሊሙ አፈቀላጤዎች የሃይማኖት ፍልስፍናውን በጥሞና ብትመረምሩትና ብታጤኑት ይመረጣል እንላችኋለን።



## የትንሣኤው ቀንና የኢየሱስ ምላሽ

ቅዱስ ቁርዓን 5 ቁ 116-118 በትንሣኤ ቀን ኢየሱስና እናቱ በመለኮታዊነት መመለካቸውን አስመልክቶ አላህ ለኢየሱስ የሚጠይቀው ጥያቄና የኢየሱስም ምላሽ ምን እንደሚሆን በሚከተለው መልኩ ተገልጧል፣ "የመርየም ልጅ ኢሳ ሆይ! አንተ ለሰዎች እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን? በሚለው ጊዜ (አስታውስ) ጥራት ይገባህ ለእኔ ተገቢዬ ያልሆነ ነገር ማለት ለእኔ አይገባኝም፣ ብየውም እንደሆነ በርግጥ አውቀሃል፣ በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፣ ግን አንተ ዘንድ ያለውን አላውቅም፣ አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም አዋቂ አንተ ብቻ ነህና፣ በርሱ ያዘዝከኝን ቃል ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ ማለትን እንጂ ለነርሱ ሌላ አላልሁም፣ በውስጣቸውም እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርሁ፣ በተመላሃኝም (ባስነሳሃኝም ጊዜ) አንተ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርህ፣ አንተም በነገር ሁሉ ላይ አዋቂ ነህ" ብሏል።

መልስ፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሕይወትም መንገድም እኔ ነኝ፣ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር አንድም ወደ አብ የሚሄድ የለም" በማለት አምላክነቱን መድኃኒትነቱን የሕይወት መንገድነቱን ገልጦ አስተምሯል፣ ዮሐ. 14 ቁ. 6፣ እናቴን አምልኩ ብሎ አልተናገረም አላስተማረም፣ የቁርዓን አፈቀላጤዎች የጨመሩት ቅጥፈት ነው፣ ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት እንደመሆኗ መጠን ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ አድርገን እናከብራታለን እናመሰግናታለን፣ በፍጻሜ ዘመን (በትንሣኤ ቀን) ቆራጭ ፈላጭ (ዋጋ ሰጭ ነሽ) የመጨረሻው ነፍስ አሰናባች የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ ያን ጊዜ ሌላ ፈራጅ ሌላ ንጉሥ የለም፣ ፍርዱም ይግባኝ የለበትም፣ ያመኑበትን ክርስቲያኖችን በቀኙ፣ ያላመኑበትን በግራው አቁሞ የሚፈርድላቸው የሚፈርድባቸው ንጉሠ ነገሥት ወልደ አብ ወልደ ማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ "እነሆ ፈጥኜ

www.ethiopianorthodox.org

እመጣለሁ፣ ዋጋዬ ከእኔ ጋራ ነው፣ ለሁሉ ለያንዳንዱ እንደሥራው መጠን እከፍለው ዘንድ”፣ ራዕይ 22 ቁ. 12።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመጨረሻይቱ ቀን (ስለትንሣኤ ሙታን) ያስተማረበት አንቀጽ አለ፣ “የሰው ልጅ (ክርስቶስ) በምስጋናው በመጣ ጊዜ ቅዱሳን መላእክት ከርሱ ጋር ያን ጊዜ በምስጋናው ዙፋን ይቀመጣል፣ አሕዛብ ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፣ እርስ በራሳቸው ይለያቸዋል፣ በጎቹን ከፍየሎች እንዲለይ፣ በጎቹን በቀኙ ያቆማል፣ ፍየሎችን ደግሞ በግራው፣ ያን ጊዜ ንጉሡ በቀኙ ያሉትን ኑ የአባቴ ቡሩካን ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ትወርሱ ዘንድ፣.... ከዚያ በኋላ ደግሞ በግራው ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል፣ እናንተ ርጉማን ከእኔ ራቁ ወደ ዘላለም እሳት ለሰይጣን እና ለመላክተኞቹ ወደ ተዘጋጀው፣..... እነዚያ ወደ ዘላለም ሥቃይ ይሄዳሉ፣ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት” ይላል፣ ማቴ. 25 ቁ. 31-46።

ያን ጊዜ የሚደረገው ልቅሶና ዋይታ አይጠቅምም እንጂ የወጉት የሰቀሉት አይሁድም ያለቅሳሉ፣ “እነሆ! እርሱ በደመና ይመጣል፣ ዓይን ሁሉ ታየዋለች፣ የወጉትም ደግሞ የምድር ነገድ ሁሉ ያለቅሳሉ፣ አዎ፣ አሜን” ራዕይ 1 ቁ. 7።

በመጨረሻ ቀንስ አይጠቅማቸውም እንጂ ሙስሊሞችም ዋጋ የሚከፍል ነቢዩ ኢሳ ነው ብለው ያምናሉ፣ አምላክነቱንና አዳኝነቱን ክደው ኖረው በመጨረሻይቱ ቀን ነፍስ አሰናባች መሆኑን ቢያምኑበት ምን ይጠቅማቸዋል? አይጠቅማቸውም።

የትንሣኤ ነገር ሲነሳ ሳይጠቀስ የማይታለፍ አንድ ቁም ነገር አለ፣ ይኸውም “ትንሣኤ ሙታን የለም” የሚሉ ወገኖች (ሰዱቃውያን) ክርስቶስን ጠይቀውት የሰጣቸው መልስ ነው፣ “መምህር ሆይ ሙሴ አንድ ሰው ቢሞት ልጅ ሳይወልድ ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ዘር (ልጅ) ይተካለት ብሏል፣ በእኛ ዘንድ ሰባት ወንድማማቾች ነበሩ፣ ታላቁ ሚስት አገባና ልጅ ሳይወልድ ሞተ፣ እንደዚሁ ሁለተኛውም ሶስተኛውም እያሉ እስከ ሰባተኛው ድረስ አገቧት፣ ሁሉም ሞቱ በመጨረሻም ሴቲቱ ሞተች፣ በትንሣኤ ቀን ከሰባቱ ለማንኛው ሚስት ትሆናለች? ሁሉም አግብተዋታልና ሲሉ ጠየቁት፣ ክርስቶስም የእግዚአብሔርን ኃይልና መጻሕፍትን ባለማወቃችሁ ተሳስታችኋል፣ ከትንሣኤ በኋላ ሰዎች አያገቡም አይጋቡምና፣ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይኖራሉ እንጂ፣ ስለትንሣኤ ሙታን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተባለውን አላነበባችሁምን? እኔ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ነኝ፣ እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም” ሲል መልሶላቸዋል፣ ማቴ. 22 ቁ. 23-32።

እንግዲህ ሞተን ተነስተን በሰማይ ሚስት አግብተን ተደስተን እንኖራለን የሚል እምነትና ተስፋ ያላቸው ክፍሎች ቢኖሩ ተሳስተዋል፣ ስህተታቸውን ዛሬውኑ ቢያርሙ ቢያስተካክሉ ይሻላቸዋል፣ ያርሙ ያስተካክሉ፣ ስህተትን ማረሚያው ይህ ዓለም ነው፣ በዚህ ዓለም ያልታረመ ስህተት በወዲያኛው ዓለም ውጤቱ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ብቻ ነው፣ ማቴ. 25 ቁ. 30።

## ከቶውንም አምላክ ነኝ አላለም

“ሁሉን አዋቂ በሆነው አላህ የተረጋገጠው “በርሱ ያዘዝከልኝን ቃል ጌታዬና ጌታችሁን አላህን ተገዙ” የሚለው የኢየሱስ ቃል ሐቅ ሆኖ ሳለ ሕዝበ ክርስቲያን እንደምን ኢየሱስን እንደ አምላክ አድርጎ ይይዛል? በፕሮቴስታንቶችና በካቶሊኮች መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ “ጌታ ነኝ” ወይም “እኔን ተገዙኝ” ብሎ የተናገረበት አንቀጽ አይገኝም፣ ኢየሱስ “እኔና አብ አንድና ተመሣሣይ ነን” ያለበት የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጽ አንድም ቦታ የለም ካለ በኋላ ጸሐፊው ባዘጋጀው የራት ግብዣ ላይ ለተገኙት ብፁዕ ሞሪስ ዳዲ ይህንኑ ጥያቄ አቅርቦላቸው ተጋባዡም “እኔና አብ አንድ ነን” የሚል ምላሽ ቢሰጡት እንደገና ተያያዥ አንቀጾችን እንዲያነቡልኝ ብጠይቃቸው ምን ማለትህ ነው? ሲሉ ዓይናቸውን አፈጠጡብኝ፣ እኔም ተያያዥ አንቀጽ ምን እንደሆነ አብራራሁላቸው” ብሏል፤


www.ethiopianorthodox.org

ይጠቀማሉ፣ በብሉይ ኪዳን ዘፀ. 7 ቁ. 1 ላይ "እግዚአብሔር ሙሴን እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ" የሚለውን ሙሴን ለማመልከት ስትጽፉ ትንሹን "ጂ" ትጽፋላችሁ ለ "ቃል" (word) ግን ትልቁን "ጂ" (G) ትጠቀማላችሁ፣ ለምን እኮ? ለምን? የአምላክን ቃል እንዳሰኛችሁ ትጫወቱበታላችሁ? ሲል ካናዳዊውን ምሁር ጠይቋል፣ እርሳቸውም "እንዴ! የእኔ እጅ እኮ የለበትም" ቢሉት የርስዎ እጅ እንደሌለበት አውቃለሁ፣ ግና እኔ የምናገረው የክርስቲያን ሸማ ለብሰው የኢየሱስን አምላክነት ስለሚሰብኩ ነው፣.... ያለአዋቂውን ሕዝብ ለማምታታትና የእውነትን ደብዛ ለማጥፋት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አያሌ ተንኮሎች መፈጸማቸውን ልናሳውቅ እንሻለን" ብሏል።

<u>መልስ፣</u> መናፍቃን ምንጊዜም አይረቱም፣ እጃቸውን አይሰጡም፣ ጸሐፊው "ክርስቶስ አምላክ ነኝ አላለም፣ አስረዱኝ" ሲል ላቀረበው ጥያቄ "አስቀድሞ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ" በማለት ዓለም ሳይፈጠር ከአብ ጋር የነበረ፣ በኋላ ዘመን ከሰማየ ሰማያት የወረደ ከድንግል ማርያም የተወለደ የአብ ቃል አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑን በሚገባ የሚያስረዳ የማያዳግም መልስ ተሰጥቶት ነበር፣ ሆኖም አሜን ብሎ አልተቀበለውም፣ "የፈለጉትን ቢያጡ ያልፈለጉትን ይቀላውጡ" እንደተባለው አሜን ብሎ በመቀበል ፋንታ የአውሮፓ ፊደሎች የአምላክ ስምና የጣዖት ስም ሲጻፍባቸው ለምን ካፒታልና እስሞል ይሆናሉ? ለምንስ የአምላክን ስም እንደፈለጋችሁ ትጫወቱበታላችሁ? ከዚህ የተነሳ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አያሌ ተንኮል ተፈጽሞበታል በማለት ተቀርቋሪ መስሎ ቀርቧል።

መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ሙስሊሙ አፈቀላጤዎች አድርጎ የተጫወተበት የለም፣ የእግዚአብሔር ስምና አምልኮት የሚለካው በፊደል ቅርፅ አይደለም፣ ፊደሎች አሳብን በቃላት ለመግለጥ ስንስለት ሆነው ያገለግላሉ እንጂ የጣዖትና የታቦት ስም መለዩ ሊሆኑ አይችሉም፣ እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀው አንድነቱንና



ሦስትነቱን አምላክነቱንና አዳኝነቱን እንድናውቅ ሕጉን ትእዛዙን እንድንጠብቅና በቅን ልቡና እንድናመልከው ነው።

www.ethiopianorthodox.org

# ስምንተኛ ምዕራፍ

## ምን ቀረ?

"ሦስት አበይት ነጥቦች በዚች አናሳ መጽሐፍ በ15 የተለያዩ የቁርዓን ክፍሎች ውስጥ ኢየሱስን በተመለከተ የቀረቡትን ማስረጃዎች በዝርዝር መዳሰስ ይቻላል ብሎ መገመት የማይታሰብ ጉዳይ ነው፣ በመሆኑም ለማድረግ የምንችለውን ያህል ዋና ዋና ነጥቦችን ከቁርዓን በማውጣት ለአንባቢ በሚያመች መልኩ ማስገንዘቢያ ዝርዝር ማቅረብ ነው፣ እስካሁን ትኩረት ያልሰጠናቸውን ሦስት ነጥቦች ማለትም

1. አልተሰቀሉትም 4 ቁ. 57፤
2. ተልዕኮውና የሠራቸው ተአምራቶች 4 ቁ. 13፣ 19 ቁ. 33፤
3. የሙሐመድን መምጣት ስለማብሰሩ (61 ቁ. 6) በዝርዝር እንመለከታለን ብሏል፤

<u>መልስ፣</u> ሙስሊሞች ከ600 ዘመን በኋላ ተነስተው ኢየሱስ አልሞተም አልተሰቀለም የሚል ክርክር ቢያነሱ ውሸታሞች ይባላሉ እንጂ እውነተኞች አይባሉም፣ "አልወረደም አልወለደም" ከሚለው ክህደታቸው የተለየ አይደለም፣ መውረድ መወለዱን የማያምኑ መናፍቃን ሞቱን ስቅለቱን ቢክዱ አያስደንቅም፣ ክርስቶስ የወረደው የተወለደው ቀደም ሲል በተነገረው ትንቢት መሠረት የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ወርሶ ለዘላለም ነግሦ ለመኖር አይደለም፣ ሊሞት ሊሰቀል መከራ ሊቀበል፣ ዓለምን ሊታደግ የጠፋውን በግ (አዳምን) ሊፈልግ ነው፣ ሞቱና ስቅለቱም ድንገት ሳይታሰብ የመጣ ዕንግዳ ደራሽ ውሃ ፈሳሽ አይደለም፣ በብሉይ ኪዳን ትንቢት ተነግሮለት በተስፋ ሲጠበቅ የቆየ ነው።



ይኸውም ነቢዩ ኢሳይያስ "በእውነት እርሱ ደዌያችንን ወሰደ፣ ሕመማችንን ተሸከመ፣ እኛም እንደተመታ ቆጠርነው፣ እግዚአብሔር እንደቀሠፈው፣ እንደተዋረደም፣ እርሱ ግን ስለኃጢአታችን ተወጋ፣ ስለዓመፃችንም ተደቀቀ፣ የደኅንነታችን ተግሣፅ በርሱ ላይ ነው፣ በርሱ ቁስለ እኛ ተፈወስን፣ እኛ ሁላችንም እንደበግ ጠፋን፣ ሁሉም ወደ መንገዱ አዘነበለ፣ የሁላችንንም ኃጢአት እግዚአብሔር በርሱ ላይ አኖረው፣ ተጨነቀ፣ ተሰቃየም፣ አፉንም አልከፈተም፣ እንደ በግ ወደ መታረድ ሄደ፣ እንደ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንዲል አፉን አልከፈተም" ይላል ትንቢቱ፣ ኢሳ. 53 ቁ. 4-7፤

"በነጋታውም ዮሐንስ ኢየሱስን ወደርሱ ሲመጣ ባየ ጊዜ እነሆ! የእግዚአብሔር በግ የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ አለ" ዮሐ. 1 ቁ. 29።

ራሱ ክርስቶስ ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ አይሁድ ሰቅለው እንደሚገድሉት ነግሯቸው ነበር፣ አይሁድ ግን አልተረዱለትም፣ "ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱና በሦስት ቀን እሠራዋለሁ" አላቸው፣ አይሁድም "ይህ ቤተመቅደስ በ46 ዓመት ተሠራ፣ አንተ ግን በሦስት ቀን ትሠራዋለህ? አሉት፣ እርሱ ግን ያላቸው "ስለ *ሥጋው* ቤተመቅደስ ነበር" ሰቅላችሁ ትገድሉኛላችሁ፣ በሦስተኛው ቀን እነሳለሁ ማለቱ ነው፣ ዮሐ. 2 ቁ. 19፣ ማቴ. 26 ቁ 61፤

የሰቀሉት የገደሉት አይሁድ በሦስተኛው ቀን እነሳለሁ ብሎ ነበርና ትንሣኤውን ከሕዝብ ለመሰወር መቃብሩን በወታደር አስጠበቁት፣ ይሁን እንጂ የነርሱ ጥበቃና ቁጥጥር ሊያስቀረው ወይም ሊገታው አልቻለም፣ ሞትን በሞቱ ደምስሶ ተነሳ፣ ጠባቂዎቹም ደንግጠው ወደቁ እንጂ ምንም ሊያደርጉ አልቻሉም፣ ትንሣኤውም ይፋ ወጣ፣ ማቴ. 28 ቁ. 1-15 ተመልከት።

እንግዲህ የሰቀሉት የገደሉት አይሁድ አልሰቀልነውም አልገደልነውም አላሉም፣ እኛም ተከታዮቹ (አማኞቹ ክርስቲያኖች)



www.ethiopianorthodox.org

2ኛ ብጠማ አጠጣችሁኝ፣
3ኛ ዕንግዳ ብሆን ተቀበላችሁ፣
4ኛ ብታረዝ አለበሳችሁኝ፣
5ኛ ብታመም ጠየቃችሁኝ፣
6ኛ ብታሰር አስፈታችሁኝ፣ ማቴ. 25 ቁ. 35፣ (5 ቁ. 3-10)

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቱና ስቅለቱ በቂ ነው ብሎ ሕጉን ትእዛዙን ከማስተማር አልተቆጠበም፣ ትእዛዛትን እንዲጠብቅ ያስተማረው ለአይሁዳዊው ጠያቂ ብቻ ሳይሆን ለደቀመዛሙርቱ ሐዋርያትም "ብትወዱኝስ ትእዛዜን ጠብቁ" ብሏቸዋል፣ ዮሐ. 14 ቁ. 15፣ ከሕግና ከትእዛዛት ውጭ ሆኜ እጸድቃለሁ ማለት በራስ ላይ መቀለድ (ራስን ማታለል ነው) ያዕ. 2 ቁ. 10፤

## ተአምራት ምንን ያረጋግጣሉ?

"ኢየሱስ (ዐ.ሰ) የሠራቸውን ተአምራት በተመለከተ ቅዱስ ቁርዓን ስለ ዕውሩ ጤሚዎስ ስለአልዓዘርም ሆነ ስለሌሎች በዝርዝር የሚያቀርበው ጉዳይ የለም፣ ግና ተወልዶ አንቀልባ ላይ ሳለ በእናቱ ላይ የተሰነዘረውን የማንጓጠጥ (የሐሜት) ጥቃት ለመከላከል የሠራውን ተአምር በዝርዝር ያቀርባል፣ እኛ ሙስሊሞች ድንቅ የሆኑ ተአምራቱን ያለምንም ማመንታት እንቀበላለን፣ ግና ክርስቲያኖች እንደሚያምኑት እነዚህ ተግባራቱ "አምላክ" ወይም "የአምላክ ልጅ" ሊያሰኙት አይችሉም፣ ተአምራት የሠሪውን ነቢይነት ሐቀኛነትም ሆነ ቅጥፈት ሊያረጋግጡ አይችሉም፣ ስለዚህ ጉዳይ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ይናገራል "ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉ፣ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስቲያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ" ብሏል፣ ማቴ. 24 ቁ. 24፤

<u>መልስ፣</u> እኛ ሙስሊሞች ኢየሱስ ያደረጋቸውን ተአምራት ሁሉ እንቀበላለን የተባለው አምላክነቱንና መድኃኒትነቱን ያልተቀበለ



www.ethiopianorthodox.org

ሙስሊም ሥራውን ቢያደንቅ ምን ይጠቅመዋል? "አጋንንትም ሥራውን ያምናሉ ይንቀጠቀጣሉም" ያዕ. 2 ቁ. 19።

ክርስቶስ በምድር ላይ ሳለ ያከናወናቸው ተግባራት ሁሉ "አምላክ ወልደ አምላክ" መሆኑን የሚያረጋግጡ ናቸው፣ በኋላ ዘመን በእኔ ስም የሐሰት ነቢያት ይነሳሉ ማለቱ ትክክል ነው፣ ሙሐመድ ግን በኢየሱስ ስም አልመጣም፣ ትምህርቱም ከትምህርቱ ጋር አይመሳሰልም፣ ስለዚህ ልዩ የፈጠራ ሰው ነው።

የሐሰት ነቢያት ልዩ ልዩ ተአምር መሥራት የሚችሉ ከሆነ ሐቀኞችን ከሐሰተኞች ነቢያት እንዴት መለየት እንችላለን? የሚል ጥያቄ ቀርቧል፣ ባንድ ወቅት ክርስቶስ ሲያስተምር ይህ ዓይነት ጥያቄ ቀርቦለት የሰጠው መልስ እንደሚከተለው ነው፣ "ተጠንቀቁ፣ ሐሰተኞች ነቢያት የበግ ለምድ ለብሰው ይመጡባችኋል፣ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ድቦች ናቸው፣ እነርሱንም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፣ ከሾህ ወይን ከአሜካላ በለስ ይለቀማልን? መልካም ዛፍ መልካም ፍሬ ታፈራለች፣ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ታፈራለች፣ መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት አትችልም፣ ክፉ ዛፍም ምልካም ፍሬ ታፈራ ዘንድ አይቻላትም፣ መልካም ፍሬ የማታፈራ ዛፍ ሁሉ ተቆርጣ ወደ እሳት ትጣላለች፣ ስለዚህ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ፣ አቤቱ አቤቱ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፤ በሰማይ ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፣ በዚያች ቀን ብዙዎች ይሉኛል፣ አቤቱ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህ ብዙ ኃይል አላደረግንምን? ያን ጊዜ እኔም እላቸዋለሁ፣ ፍፁም አላውቃችሁም፣ ከእኔ እራቁ እናንተ ኃጢአት የምትሠሩ" ሲል ይመልስላቸዋል፣ መልሱ "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ" የሚለው ነው፣ ማቴ. 7 ቁ. 15-23።

የጽሑፉ አዘጋጅ "ሴቶች ከወለዷቸው መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሳም" የሚለውን ጥቅስ ጠቅሶ መጥምቁ ዮሐንስ ከሙሴ ከዳዊት ከሰሎሞንና ከሌሎችም ነቢያት እንደዚሁም ከራሱ ከኢየሱስ እንደሚበልጥ ራሱ ኢየሱስ መስክሯል ሲል ንባቡን

በጅምር ቆርጦ አስቀርቶታል፣ የጀመረውን እንቀጽ ቢዘልቀው ኖሮ "በመንግሥተ ሰማያት ግን የሚያንሰው ይበልጠዋል" ይላል፣ "በመንግሥተ ሰማያት ግን የሚያንሰው ይበልጠዋል" መወለዱን መጥምቁ ዮሐንስ ከክርስቶስ 6 ወር ቀድሞት መወለዱን እናስታውሳለን፣ በመንግሥተ ሰማያት ግን የሚያንሰው ይበልጠዋል ማለት በመንግሥተ ሰማያት ማዘዝ መናዘዝ (ማስገባት ማስወጣት) የሚችል በልደት 6 ወር የሚያንሰው ክርስቶስ ከመጥምቁ ዮሐንስ ይበልጣል ማለት የመንግሥተ ሰማያት ባለቤት ነው ማለት ነው፣ ማቴ. 11 ቁ. 11።

"ተአምራት የማንነት ደረጃ መግለጫ ሊሆን አይችልም፣ ሙሴ ደረቁን እንጨት ሕይወት እንዲዘራ አድርጓል፣ ኤልሳዕ ሙት አስነስቷል" ተብሏል፣ ይህ ሁሉ የክርስቶስ ተበላላጭ ባልንጀራ ለማግኘት ነው፣ ክርስቶስ ከአዳም ጀምሮ ለተነሱት አበውና ነቢያት የሥራ መሪያቸው የኃይል ምንጫቸው ፈጣሪያቸው ነው፣ "አብርሃም አባታችሁ ቀኔን ያይ ዘንድ ተመኘ፣ አይቶም ደስ አለው ቢላቸው አይሁድ ገና አምሳ ዓመት አልሞላህ አብርሃምን እንዴት አየሁ ትላለህ? አሉት፣ አብርሃም ሳይወለድ አለሁ ቢላቸው ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ" ይላል፣ ዮሐ. 8 ቁ. 56-58፣

"ኃይሉ ሁሉ የርሱ አይደለም የተውሶ ኃይል ነው" ተብሏል፣ ለማስረጃ የተጠቀሰው "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አልችልም፣ እንደሰማሁ እፈርዳለሁ እንጂ" "እኔ ለራሴ የምመሰክር አይደለሁም፣ የላከኝ አብ ይመሰክርልኛል እንጂ" "በእኔ ባታምኑ በሥራዬ እመኑ እንድታውቁ እንድታምኑም፣ አብ በእኔ እንዳለ እኔም በአብ" ማቴ.28 ቁ. 18፣ ዮሐ. 5 ቁ. 30፣ ዮሐ. 8 ቁ. 18፣ ዮሐ. 10 ቁ. 38፣ .... ከዚህ በላይ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል፣ ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ኃይለ ቃሎች ክርስቶስ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በባሕርይ በመፍጠር በመግዛትና በፈቃድ አንድ መሆናቸውን መናገሩ ነው እንጂ አባቴ ከእኔ ይበልጣል እኔም ከአባቴ አንሳለሁ ማለቱ አይደለም፣ "እኔና አብ አንድ ነን" ማለት እኩል ነን፣ ተመሳሳይ ነን ማለቱ ነው።


www.ethiopianorthodox.org

## የአልዓዛር ትንሣኤ

"አልዓዛር በታመመ ጊዜ እህቶቹ ማርያምና ማርታ ይፈውስላቸው ዘንድ ወደ ኢየሱስ ላኩበት፣ ኢየሱስም በሰማ ጊዜ ይህ ደዌ ለሞት አይደለም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ በርሱ ይመሰገን ዘንድ ነው፣..... አለና ወንድማችን አልዓዛር ተኝቷል፣ አስነሳው ዘንድ እሄዳለሁ አላቸው ለደቀመዛሙርቱ፣ ደቀመዛሙርቱም ስለእንቅልፍ የተናገረ መስሏቸው ከተኛ ይነሳል አሉት፣ በኋላ ግን መሞቱን ገልጦ ነገራቸውና፣ .......ቢሄዱ አልዓዛር ከሞተ አራት ቀን ሆኖታል፣ ...... ማርታ ኢየሱስ መምጣቱን ስትሰማ ልትቀበለው ወጣች፣ ጌታ ሆይ! ከዚህ ብትኖር ኖሮ ወንድሜ ባልሞተም ነበር አለችው፣........ወንድምሽ ይነሳል አላት፣ ማርታም ኋላ በትንሣኤ ቀን እንደሚነሳ አውቃለሁ አለችው፣ ኢየሱስም እኔ ነኝ ትንሣኤ ሕይወትም፣ ያመነብኝ ቢሞትም ይድናል አላት፣.......አዎ ጌታ ሆይ! እኔ አምናለሁ፣ አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ ወደ ዓለም ይመጣ ዘንድ ያለው አለችው፣ ማርታም ማርያምን ጠርታ አመጣቻት፣ ማርያምም እያለቀሰች በእግሩ ላይ ወድቃ ጌታ ሆይ! ከዚህስ ኖረህ ቢሆን ወንድሜ ባልሞተ ነበር አለችው፣ ኢየሱስም ስታለቅስ ባየ ጊዜ በልቡ አዘነ፣ እራሱን እየነቀነቀ ወዴት ቀበራችሁት? አለና .... ወደ መቃብሩ ሄደ፣ ..... መቃብሩ በድንጋይ ተገጥሞ ነበር፣ ኢየሱስ ድንጋዩን አንሱ አላቸው፣ ማርታም ጌታ ሆይ! ፈጽሞ ተልቷል፣ አራት ቀን እኮ ሆኖታል አለችው፣ ኢየሱስም አልነገርኩሽምን? ካመንሽ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታይ አላት፣ ድንጋዩንም አነሱ፣ ኢየሱስ ዓይኖቹን ወደላይ አነሳና አባት ሆይ! አመሰግንሃለሁ ሰምተኸኛልና፣ እኔም አውቃለሁ ሁልጊዜ እንደምትሰማኝ ስለነዚህ ስለቆሙት ሰዎች አልሁ፣ ያምኑ ዘንድ አንተ እንደላከኸኝ ካለ በኋላ ድምፁን ከፍ አድርጎ አልዓዛር አልዓዛር ና ወደውጭ ውጣ አለው፣ አልዓዛርም ከመቃብሩ ወጣ፣ እጆቹና እግሮቹ በከፈን እንደተጠቀለሉ፣ ኢየሱስም ፍቱትና ይሂድ አላቸው፣ አይሁድም ኢየሱስ ያደረገውን ተአምር አይተው አመኑበት" ዮሐ. 11 ቁ 1-45።

<u>መልስ፣</u> ጸሐፊው አዛብቶ ያቀረበውን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አልዓዛርን ከሞት ያስነሳበትን ታሪክ አንብባችሁ ታመዛዝኑ ዘንድ ሳይሸራረፍ እንዳለ አቅርቤዋለሁ፣ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የክርስቶስ አምላክነት ጎልቶ ከሚታወቅባቸው አያሌ አስደናቂ ተግባሮች አንዱ ይህ የአልአዛር ትንሣኤ ነው፣ ክርስቶስ የወዳጁን የአልዓዛርን መታመም ከሰማ ካራት ቀን በኋላ ዘግይቶ ነው የደረሰው፣ እህቶቹ ሞቶ የሚቀር ስለመሰላቸው አልዓዛር ሳይሞት ኢየሱስ ደርሶ እንዲፈውስላቸው ምኞታቸው ነበር፣ ክርስቶስ ግን አልዓዛር ከሞተ በኋላ ዘግይቶ መድረሱ ሬሳውን አስነስቶ ተቃዋሚዎቹን አይሁድ በተግባር ማሳመን ነበረበት፣

"አባት ሆይ! አመሰግንሃለሁ ሰምተኸኛልና፣ ሁልጊዜ እንደምትሰማኝ አውቃለሁ" የሚሉት ቃላት የክርስቶስን አምላካዊ ባሕርይ ዝቅ የሚያደርጉ አይደሉም፣ ከአብ ጋር ያለውን መለኮታዊ አንድነትና ፈቃድ የሚያመለክቱ ናቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ አብና መንፈስ ቅዱስ ሥጋ ባለመልበሳቸው አይታዩም አይዳሰሱም፣ ወልድ ግን የእኛን ሥጋ በመልበሱ በዓይን ይታያል፣ በእጅ ይዳሰሳል፣ ሰው እንደመሆኑ መጠን በሥጋ ባሕርይ "እለምንሃለሁ አመሰግንሃለሁ" የሚል ቃላት ማሰማቱ አምላካዊ ባሕርዩን አይለውጠውም፣ ይህ ሁሉ ከአብ ጋር ያለውን የፈቃድና የሥልጣን አንድነት የሚያስረዳ እንጂ የተውሶ ኃይል አይባልም፣ አብ ሙታንን እንዲያስነሳ እንዲያድናቸውም እንዲሁ ልጅም ደግሞ የወደደውን ያድናል፣ ዮሐ. 5 ቁ. 21፣

> "የመጽሐፉ ሰዎች ባመኑ ኖሮ ለነሱ በተሻላቸው ነበር፣ ከነሱ አማኞች አሉ፣ አብዛኞቻቸው ግን አመፀኞች ናቸው" ተብሏል፣ ቁርዓን 3 ቁ. 110፣

<u>መልስ፣</u> በቁርዓን ውስጥ የመጽሐፉ ሰዎች የሚባሉት አይሁዶችና ክርስቲያኖች ናቸው፣ ቁርዓን አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን ከሐዲዎች (አመፀኞች) ይላቸዋል፣ ከባድ ስህተት ነው፣ ከሁሉ በፊት እግዚአብሔርን ያወቁ፣ እግዚአብሔርም ያወቃቸው፣ መሪ ፈታውራሪ የሾመላቸው ሕጉን ትእዛዙን የሰጣቸው አይሁዶችና



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያኖች ናቸው፣ ይህ መሆኑ እየታወቀ እንዴት ከሐዲዎችና ዓመፀኞች የሚል ስም ተሰጣቸው? እስልምናን ያልተቀበለ ሁሉ ከሐዲ ነው ማለት ታላቅ ድንቁርና ነው፣ ከሐዲስ የክርስቶስን አምላክነትና አዳኝነት ያልተቀበለ ነው።

በዝርዝር ለማወቅ ካስፈለገ አይሁድ ከሁሉ አስቀድመው በሙሴ መሪነት ለሰው ልጆች ሁሉ መመሪያ የሆኑትን 10 ትእዛዛት (ሕገ ኦሪትን) ከእግዚአብሔር የተቀበሉ አማኞች ናቸው፣ ክርስቲያኖችም ቀደም ሲል ሕገ ኦሪትን ለሙሴ የሰጠው፣ በኋላም ሕገ ኦሪትን አሻሽሎ ሕገ ወንጌልን ለመተካት ወደዚህ ዓለም የመጣውን መሢሕ ክርስቶስን የተቀበሉ በወልድ ውሉድ፣ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባሉ በእምነታቸው ነውር ነቀፋ የሌለባቸው የፀዱ አማኞች ናቸው።

"ኦሪትንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፣ ልፈጽማቸው ነው እንጂ፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ አንዲት የውጣ (ከ10 ቃላት አንዲት ትእዛዝ) እታልፍም ሁሉ እስኪሆን ድረስ፣ ከነዚህ ትእዛዛት አንዲቱን የሻረ ወይም ለሰው ያስተማረ በመንግሥተ ሰማያት ታናሽ ይባላል፣ ይህን ያላደረገ ወይም ያላስተማረ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል" ብሏል፣ እንግዲህ አስቀድሞ በደብረሲና ሙሴን ቃል በቃል እያነጋገረ ሕገ ኦሪትን የሰጠ፣ በኋላም ሥጋ ለብሶ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ሕገ ወንጌልን ያስተማረ የሁለቱም ሕጎች ሠሪና ፈጣሪ የመንግሥተ ሰማያት ባለቤት ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ከዚህ በላይ የተሰጠውን ግልጥ መመሪያ አመዛዝናችሁ ትፈርዱ ዘንድ ለአንባቢዎች ትቸዋለሁ፣ ማቴ. 5 ቁ. 17-19፤

ቁርዓንም ከዚህ በላይ የተነገረውን ቁም ነገር የሚያጠናክር መልእክት አለው፣ "በፈለጎቻቸው (በነቢያቶቹ ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ኢሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከተልን፤ ኢንጅልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም (ኦሪትን) የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆች መሪና ገሣጭ ሊሆን ሰጠነው" ይላል ቁርዓን 5 ቁ. 46፣ ይህንም ለማብራራት

"በነቢያት መንገድ የመጣው የማርያም ልጅ ኢየሱስ ከኦሪት በፊት የነበረውን (ሕገ ልቡና) ገላጭ፣ በርሱም ጊዜ ያለችውን ኦሪትን የሚያረጋግጥ፣ ለጥንቁቶች (ለክርስቲያኖች) መሪና ገሣጭ በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበትን ወንጌልን ሰጠነው" ማለት ሲሆን፣ እንግዲህ ወንጌልም ሆነ ቁርዓን የሰጡት ተመሳሳይ ማስረጃ ክርስቶስ የወንጌል ባለቤት ብቻ ሳይሆን ከኦሪት በፊትም ለነበረው (ሕገ ልቡና) ገላጭ፣ ከዚያም የኦሪትና የነቢያት ፈጻሚ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ታዲያ ቁርዓንና ወንጌል እንደዚህ ሐቁን እየመሰከሩ እኛ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ለምን ድብብቆሽ እንጫወታለን?

"ከቶ ትንቢት በሰው ፈቃድ አለመጣችም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሯት"፣ 2 ጢሞ. 3 ቁ. 16፣

## ማስታወሻዎች

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ በመጨረሻ ካስፈራቸው ማስታወሻዎች ለጥቂቶቹ ቀደም ሲል መልስ ተሰጥቶባቸዋል፣ ለቀሩትም እንዳለፉት ክፍሎች ሙሉ ቃላቸውን ሳልጽፍ አልፎ አልፎ መልስ ለሚያስፈልጋቸው ብቻ ባጭር ባጭሩ ፍሬ ነገሩን እየወሰድሁ መልስ ሰጥቻባቸዋለሁ፣ መልስ የሚያስፈልጋቸውን በፊደል ተራ አስቀምጫቸዋለሁ፣

ሀ) "ኢየሱስ (ኢሳ) ከነርሱ ክህደት በተሰማው ጊዜ ወደ አላህ ረዳቶቼ እነማን ናቸው? አለ፣ ሐዋርያት እኛ የአላህ ረዳቶች ነን፣ በአላህ አምነናል፣ እኛም ትክክለኛ ታዛገዮች መሆናችንን መስክር አሉ፣ ጌታችን ሆይ! ባወረድኸው (በቁርዓን) አመንን፣ መልክተኛውንም ተከተልን፣ ከመስካሪዎችም ጋር መዝግበን አሉ፣ "ወደ ሐዋርያትም በእኔና በመልክተኛዬ እመኑ በማለት ባዘዝሁ ጊዜ (አስታውስ) አመንን፣ እኛም ሙስሊሞች መሆናችንን መስክር" አሉ ይላል፣ ቁርዓን 3 ቁ. 52-53፣



<u>መልስ፣</u> የሙስሊሙ ኅብረተሰብ አፈቀላጤዎች በክርስትና ሕይወት ላይ የማይሸርቡት ሴራ የማያቀርቡት የሐሰት ፈጠራ የለም፣ አሁን ደግሞ ሐዋርያት ሙስሊሞች ናቸው ብለው ጽፈዋል፣ አስገራሚ ፈጠራ ነው፣ ኢየሱስን ለምን ለይተው ተውት? የውሸት ግማሽ ምን ያደርግላቸዋል? ለምን አስልሟል አላሉም? አንዱ ለባልንጀራው "በድፍን ቅል አይጥ ገብታ አየሁ አለው፣ እንዴት አድርጋ ቢለው ጉዱስ የት ላይ ነው? በማለት ስቆ አሳቀው" ይባላል፣ ከክርስትና ምስረታ ከ600 ዓመተ ምሕረት በኋላ ሐዋርያት አስልመዋል (እስልምናን ተቀብለዋል) ብሎ ማውራት "በድፍን ቅል አይጥ ገብታ" የተባለው ዓይነት ተረት ነው፣ ሌላ ሐተታ አያስፈልገውም፣ "ወዮላችሁ! እናንተ ጻፎች ግብዞች በሰው ፊት መንግሥተ ሰማያትን የምትዘጉ፣ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም ትከለክላላችሁ" ማቴ. 23 ቁ. 13።

ለ) "እኛ የአላህን መላክተኛ የመርያምን ልጅ አልመሢህ ኢሳን ገደልን በማለታቸው ረገምናቸው፣ አልተገደሉም አልተሰቀሉም፣ ግን ለነሱ የተገደለው ሰው በኢሳ ተመሰለ፣ በነገር የተለያዩት ከርሱ መገደል በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፣ ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገር ምንም ዕውቀት የላቸውም፣ በእርግጥ አልገደሉትም፣ ይልቁንስ አላህ ወደሱ አነሳው፣ ......" ይላል፣ ቁርዓን 4 ቁ. 157-159

<u>መልስ፣</u> የሞቱና የስቅለቱ ታሪክ በምዕራፍ 8 ላይ "ምን ቀረ" በሚል ንዑስ ክፍል ውስጥ በሰፊው የተብራራ ስለሆነ ከዚህ መድገም አያስፈልግም፣ ነገር ግን በቁርዓን ውስጥ እርስ በርሳቸው የሚጋጩ አንቀጾች ይነበባሉ፣ ቀደም ሲል ኢየሱስ በሕፃንነቱ የተናገረው ነው ተብሎ በምዕራፍ 19 ቁ. 32-33 "...ለእናቴ ታዛዥ አድርጎኛል፣ ትዕቢተኛ እምቢተኛም አላደረገኝም፣ ሰላም በእኔ ላይ ነው፣ በተወለድሁ ቀን በምሞትበትም ቀን ሕያው ሆኜ በምቀሰቀስበትም ቀን" ይላል፣ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው አንቀጽ ደግሞ "አልሰቀሉትም አልገደሉትም" ይላል፣ እንግዲህ ቁርዓን እንደሚለው ኢየሱስ



www.ethiopianorthodox.org

በሕፃንነቱ በራሱ እንደበት "እሞታለሁ ሕያው ሆኜ እቀሰቀሳለሁ" ካለውና አፈቀላጤዎች ደግሞ "አልሞተም አልተሰቀለም" ከሚሉት የትኛው ነው የሚታመነው? ፍርዱን ለአንባቢዎች ትቸዋለሁ።

ሐ) "አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው አለች፣ ክርስቲያኖችም አልመሢሕ የአላህ ልጅ ነው አሉ፣ ይህ ባፎቻቸው የሚናገሩት ቃሎቻቸው ነው፣ የነዚያን ከነሱ በፊት የካዱትን ሰዎች ቃል ይመሳሰላሉ፣ አላህ ያጥፋቸው፣ ከእውነት እንዴት ይመለሳሉ?" ይላል ቁርዓን 9 ቁ. 30፣

<u>መልስ፣</u> አይሁድ ዑዘይር የሚባል ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብለው የተነሱበት ጊዜ የለም፣ እኛ ክርስቲያኖች ግን "ይወርዳል ይወለዳል" ተብሎ በአራት በነቢያት ትንቢት የተነገረለት ሱባዔ የተቆጠረለት የሰው ልጅ ሁሉ በተስፋ ይጠባበቀው የነበረው መሢሕ ክርስቶስ መሆኑን አምነን ተቀብለን በስሙ ተጠምቀን የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል፣ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል፣ ያላመነ ያልተጠመቀ ግን ይፈረድበታል" ማር. 16 ቁ. 16፣

መ) "አላህም የመርየም ልጅ ኢሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብልሃልን?" የሚል ጥያቄ ይነበባል፣

<u>መልስ፣</u> ቀደም ሲል በምዕራፍ 6 "የትንሣኤው ቀን" በሚል ንዑስ ክፍል ይኸው ዓይነት ጥያቄ ቀርቦ በቂ መልስ ተሰጥቶበታል፣ በዚህ ላይ ክርስቶስ ስለእናቱ የተናገረው ቢኖር በመስቀል ላይ ሳለ እናቱንና የሚወደውን ደቀመዝሙር ባየ ጊዜ "እነሆት! ልጅሽ እነኋት! እናትህ" በማለት ዮሐንስን ለማርያም፣ ማርያምን ለዮሐንስ አደራ መስጠቱን እናውቃለን፣ ከዚህ ውጭ የተናገረው ነገር የለም ፣ ዮሐ. 19 ቁ. 26፣

ሠ) "የመርየም ልጅ ኢሳም የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊት ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኃላ የሚመጣው መላክተኛ ስሙ አህመድ በሆነው የማበስር



ስሆን ወደ እናንተ የተላክሁ የአላህ መላክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ) በግልጥ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልጥ ድግምት ነው አሉ" ይላል፣ ቁርዓን 61 ቁ. 6።

<u>መልስ፣</u> የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእኔ በኋላ አህመድ የሚባል ሰው ይመጣል ብሎ አላበሰረም አልተናገረም፣ ይህ የአፈቀላጤዎች ልብ-ወለድ ትንቢት ነው፣ ካሁን በፊት ክርስቶስ "አጽናኝ መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ" ሲል ለሐዋርያት የሰጣቸውን ተስፋ በማዛባት ለሙሐመድ የተነገረ ትንቢት አስመስላችሁ አቅርባችሁት እንደነበር ይታወሳል፣ አሁን ደግሞ ከዚህ ስሙን ለወጥ አድርጋችሁ አህመድ ብላችሁታል፣ ከዚህ ሁሉ ራስን መቻል በራስ እግር ቆሞ መራመድ አይሻልም? ለምን ሰው ሠራሽ አካል ትፈልጋላችሁ?

መሪያችሁ ሙሐመድ የሰጣችሁ ቁርዓን ስፊ ሁዳድ ነው፣ ለእኛም መሪያችን ክርስቶስ ያወረሰን ወንጌል ስፊ ቀላድ ነው፣ ለምን ድንበር ጥሳችሁ ወሰን አልፋችሁ ሞፈር ዘመት (መገዛዛ) ታርሳላችሁ? ለምን የሰው ይዞታ ታበላሻላችሁ? እኛ ክርስቲያኖች ግን ይህን አድርገነው አናውቀም፣ በራሳችን ሁዳድ ተወስነን በዕርፈ መስቀል አርሰን ምርጥ ዘር ወንጌልን ዘርተን ለመላው ዓለም የሚበቃ ምርት አምርተን ተመግበን ሌላውንም መግበን እንኖራለን፣ ድንበር ዘሎ የሌላውን ሳይከጅሉ በራስ ተማምኖ ራስን ችሎ መኖር ማለት ይህ ነው፣ አንገት የተሠራው ራስን ለመሸከምና አዙሮ ለማየት ነው።

"ቀራጮች ሊጠይቁት መጡ እንዲህ ሲሉ መምህር ሆይ! ምን እንሥራ? እርሱም አላቸው፣ ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ፣ ጭፍሮችም መጥተው ጠየቁት እንዲህ ሲሉ እኛ ደግሞ ምን እናድርግ? እርሱም አላቸው፣ በማንም ላይ ግፍ አትሥሩ፣ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ፣ ደመወዛችሁ ይበቃችኋል" ሉቃ. 3 ቁ. 10-14።

www.ethiopianorthodox.org

## ማጠቃለያ

የቁርዓኑ ምሑራን መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር በቃላችሁ ሸምድዳችሁታል፣ በውስጡም የሚያማልሉ ጥቅሶችን አንብባችኋል፣ በተለይ ሐዲስ ኪዳን በውስጡ የሌሎች ግለሰቦች ታሪክ የለበትም፣ የክርስቶስ ታሪክ ብቻ ነው፣ መሢሕ ክርስቶስ ወረደ ተወለደ፣ ሞተ ተሰቀለ፣ በሶስተኛው ቀን ተነሳ፣ ወደ ሰማይ ዓረገ ባባቱ ቀኝ ተቀመጠ፣ ወረደ ተወለደ ሙት ተሰቀል ብሎ አባቴ ልኮኛል፣ እኔና አብ አንድ ነን፣ እኔን ያየ አብን አየ የሚሉ የሁለቱን አንድነትና ተመሳሳይነት አልፎ አልፎ ሦስትነታቸውን ማለት መንፈስ ቅዱስን ጨምሮ የሚገልጡ አያሌ አንቀጾች አንብባችኋል፣ ይሁን እንጂ ሐቁ አይዋጥላችሁም፣ የሸምደዳችሁ ዋና ዓላማ ለንጽጽር ሳይሆን ከውስጡ ነውር ነቀፋ አግኝቶ መጽሐፋችሁ እንዲህ ይላል እያሉ ለመተቸት ብቻ ነው፣ ትችት ደግሞ ወደ እግዚአብሔር ቤት አያደርስም፣ የእግዚአብሔርን ቤት ይዘጋል እንጂ "ወዮላችሁ! እናንተ ጻፎች ግብዞች በሰው ፊት መንግሥተ ሰማያትን የምትዘጉ፣ እናንተ አትገቡም፣ የሚገቡትንም ትከለክላላችሁ" ማቴ. 23 ቁ. 13።

አንድ ነገር አስገኝ (ፈጣሪ) አለው፣ ቤት ያለሰሪ ፍጡር ያለፈጣሪ አይገኝም፣ የወንጌል ሥር መሠረቱ ኦሪትና ነቢያት ናቸው፣ የኦሪትና የነቢያት ፈጻሚያቸው ደግሞ ክርስቶስ ነው፣ "ነቢያት በመደመዱ ሐዋርያት ገደገዱ" ማለት ነቢያት መሢህ ክርስቶስ ይወርዳል ይወለዳል ብለው ትንቢት ተናገሩ፣ ሐዋርያት ደግሞ ወረደ ተወለደ ብለው ዓለምን ዞረው አስተማሩ።

የክርስትና ሃይማኖት ምሰሶዎች መምህራን ናቸው ማለት ማቴዎስ ማርቆስ ሉቃስ ዮሐንስ ጳውሎስና ሌሎችም ሐዋርያት ናቸው፣ ግድግዳው ጨፈቃና ማገሩ ሊቃውንትና የጻፏቸው መጻሕፍት ሲሆኑ ጭቃ መለሰኛው ደግሞ ምዕመናን ናቸው፣ "ስለዚህ ነገሬን የሚሰማ የሚያደርገውም ቤቱን በጭንጫ ላይ የሠራ ብልህ ሰውን ይመስላል፣ ዝናም ዘነመ፣ ጎርፍ ጎረፈ፣ ነፋስም ነፈሰ፣ ያንንም ቤት መታው፣ አልወደቀም፣ በጭንጫ ላይ ተመሥርቷልና" ማቴ. 7 ቁ. 24።

ኢየሱስ ወደ ቂሳርያ በመጣ ጊዜ ሰዎች ስለእኔ ምን ይላሉ? ሲል ደቀመዛሙርቱን ጠየቀ፣ እነሱም መጥምቁ ዮሐንስ ነው፣ ግማሹ ኤልያስ ነው፣ ግማሹ ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል አሉት፣ እርሱም እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ? አላቸው፣ ሲሞን ጴጥሮስም አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ አለው፣ ኢየሱስም የዮና ልጅ ሲሞን ሆይ! ምሥጉን ነህ ሥጋና ደም አልገለጠልህምና፣ ነገር ግን የሰማዩ አባቴ ገለጠልህ እንጂ፣ እኔም እልሃለሁ አንተ አለት ድንጋይ ነህ፣ በዚች ድንጋይ ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ፣ የገሐነም አበጋዞች (መናፍቃን) ሊያናውጧት አይችሉም" ማቴ. 16 ቁ. 16-18።


www.ethiopianorthodox.org

# መደምደሚያ

## የመልስ መጻሕፍቱ የተዘጋጁበት ምክንያት

አቶ በቀለ ሀብተ ወልድና ወ/ሮ ሂሩት መኮንን የተባሉ የመንፈስ ቅዱስ ልጆች አሉኝ፣ ሰባት ልጆች ወልደው ሁለቱ ጠፍተውባቸዋል፣ አንጋፋው ልጃቸው የቀይ ሽብር ሰለባ ሆኖ ሲቀር ሁለተኛዋ ሴት ልጃቸው ደግሞ በሕመም ምክንያት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች፤ የክፉ ቀን ወዳጆቹ ወግ ደርሷቸው ሶስተኛውን ልጃቸውን ሲድሩ የደስታቸው ተካፋይ እንድሆን ተጠርቼ አዲስ አበባ በመጣሁበት ወቅት የክርስትናን ሃይማኖት የሚነቅፍ እስላማዊ መጽሐፍ ታትሞ መሰራጨቱን ሰማሁ፣ ምናልባት መልስ ተሰጥቶበት እንደሆነ ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሄጄ ብጠይቅ እንዳንዶቹ እንኳን መልስ ሊሰጥበት መጻፉንም አናውቅም አሉኝ፣ አንድ የሊቃውንት ጉባኤ አባል የሆነ ወዳጄ እመንገድ ላይ አግኝቼ ብጠይቀው መልስ እንድንሰጥበት መጽሐፉ ቀርቦልን ነበር፣ ነገር ግን የጉባኤው ሰብሳቢ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ትተውን ሄዱ ካለኝ በኋላ እንዲያውም እርስዎ መልስ ይስጡበት እኔ መጽሐፍቱን ገዝቼ እሰጥዎታለሁ አለኝ፣ እኔም ብዙ ዋጋ የሚጠይቅ ከሆነ እነግርሃለሁ አልሁና መጻሕፍቱ ወደሚገኙበት አካባቢ ሄጄ አራቱን መጻሕፍት በቀላሉ ሸምቼ ተመለስሁ።

የተጠራሁበትን የደስታ በዓል ከወዳጆቼ ጋር ከተካፈልሁ በኋላ ግንቦት 2 ቀን 1988 ዓ.ም. ወደ ጅንካ ተመልሼ ወዲያውኑ መጻሕፍቱን በጥሞና እያነበብሁ ከቀላሉ ጀምሬ የመልስ ጽሑፌን ተያያዝሁት፣ የአራቱንም መጣጥፎች የመልስ ጽሑፍ ጥቅምት 30 ቀን 1989 ዓ.ም. አከናውኜ ፈጸምሁ፤ የመልስ መጻሕፍቱን እንድጽፍ ያነሳሳኝና የገፋፋኝ እግዚአብሔር እንደነበረ አልጠራጠርም፤ የመልስ መጻሕፍቱን ሌሊትና ቀን ነው የጻፍኋቸው፣ ድካም አልተሰማኝም፣ የአይን መደፍረስም ሆነ የአእምሮ መሰልቸት አልደረሰብኝም፣ ሌላው ቀርቶ የምሳና የእራት ጊዜ አላከብርም ነበር፣ አጋጣሚ ሆኖ በዚያ ወቅት የከተማው ሕዝብ ኤሌክትሪክ የሚያገኘው በየሦስቱ ቀን በፈረቃ ስለነበረ ኤሌክትሪክ በሌለበት ምሽት በሻማ እጽፍ ነበር።

የመልስ ጽሑፉ ከተዘጋጀ አሳታሚ እንደማይቸግረኝ ባለሙሉ ተስፋ ነበርሁ፣ ምክንያቱም ቀደም ሲል መጻሕፍቱን ገዝቼ በተመለስሁ ጊዜ ባሕታዊ ገብረ መስቀልን አነጋግሬአቸው መጻሕፍቱ ከተዘጋጁ እንደሚያሳትሟቸው ቃል ገብተውልኝ ስለነበረ ነው፤ ይሁን እንጂ በታሕሣሥ ወር 1989 ዓ.ም. የመልስ ድርሰቶቹን ይዤ ወደ አዲስ አበባ መጥቼ ሳለሁ በጥር ወር 1989 ዓ.ም. በቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ከተገደሉት ባሕታዊ ፈቃደ ሥላሴ ጋር በተያያዘ ምክንያት ባሕታዊ ገብረ መስቀልም ስለታሰሩ መጻሕፍቱን ለማሳተም የነበረኝ ብሩህ ተስፋ ደበዘዘ፣ ከዚህ በኋላ የሌሎችን በጎ አድራጊዎች በር ማንኳኳት ጅመርሁ።

በበጎ አድራጎት ተግባራቸው ከታወቁት አንዷን ወይዘሮ ለማነጋገር እቤቷ ድረስ ሄጄ ባጋጣሚ አላገኘኋትም፣ ስልክ ቁጥሯን ይዤ ተመለስሁና በማግስቱ ጧት ስልክ ደውዬ ቀጠሮ እንድትሰጠኝና በግንባር ቀርቤ እንዳነጋግራት ፈቃዷን ብጠይቅ እያለቀሰች ለማነጋገር ፈቃደኛ አልሆነችም፤ በዚያ ወቅት በባሕታዊው ሞት ምክንያት ልቡ በሐዘን ያልተነካ ምዕመን አልነበረም፤ በዚሁ ዓመት በጎ አድራጊዎችን ለማግኘት ከጅንካ አዲስ አበባ ሦስት ጊዜ ተመላልሻለሁ፣ ደግነቱ ለአምላክ ምስጋና ይግባውና ለትራንስፖርት እጃቸውን የሚዘረጉ ሰዎችን አላሳጣኝም፣ በመጨረሻም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሲሆን በጎ አድራጊውን ምዕመን ጅንካ ድረስ ሰተት አድርጎ ላከልኝ።

"አቤቱ ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ፣ የፀናውንም መንፈስ በውስጡ አሳድር፣ ከፊትህ አትጣለኝ ቅዱስ መንፈስህንም አትውሰድብኝ፣ የማዳንህን ተስፋ መልስልኝ፣ በጽኑ መንፈስህም ደግፈኝ፣ ለሕግ ተላላፊዎች መንገድህን አስተምር ዘንድ፣ አዳኝነትህን የዘነጉ ወደአንተ ይመለሱ ዘንድ" መዝ. 51 ቁ. 10-13።

እንደዚሁም "ከዚህ መንጋ ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፣ አመጣቸው ዘንድ ሥልጣን አለኝ ... በጎችም ለአንድ እረኛ አንድ መንጋ ይሆናሉ" ስትል ለክርስትናው ዓለም የሰጠኸውን አምላካዊ ተስፋ ትፈጽምልን ዘንድ ዘወትር በጸሎት እንጠይቅሃለን፣ አሜን፤

"ወስብሐት ለእግዚአብሔር"
አነሳስተው ላስጀመሩኝ፣
አስጀምረው ላስፈጸሙኝ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ክብር ምስጋና ይገባቸዋል፣ አሜን።


www.ethiopianorthodox.org

